ኮሮናቫይረስ እና ክርስቶስ



ጆን ፓይፐር

ኮሮናቫይረስ

እና

ክርስቶስ

ኮሮናቫይረስ እና ክርስቶስ

ጆን ፓይፐር

CROSSWAY®
WHEATON, ILLINOIS

መጀመሪያ በእንግሊዝኛ ከተጻፈው መጽሐፍ የተተረጎመ

Translated from the original English language edition.

Coronavirus and Christ
Copyright © 2020 by Desiring God Foundation
Published by Crossway
1300 Crescent Street
Wheaton, Illinois 60187

All rights reserved. No part of this publication may be reproduced, stored in retrieval system, or transmitted in any form by any means, electronic, mechanical, photocopy, recording, or otherwise, without the prior permission of the publisher, except as provided for by USA copyright law. Crossway® is a registered trademark in the United States of America.

Coronavirus and Christ is translated in Amharic by Gerji Emmanuel United Church Ethiopia.

Revised and edited by Spread of Grace Ministries, United States

First Amharic eBook Publishing: 2020

This Amharic translation book is published in digital format in collaboration with Spread of Grace Ministries.

Unless otherwise indicated, Scripture quotations are from the New Amharic Standard Version (NASV) Bible.

All emphases in Scripture quotations have been added by the author.

Coronavirus and Christ Amharic edition eBook ISBN: 978-1-952850-03-5



Spread of Grace Ministries (SGM) exists to extend the reach of the grace of God to the nations of the world by equipping national church pastors and leaders to study, believe, and preach the Bible and to strengthen the local church.

መጀመሪያ በእንግሊዝኛ ከተጻፈው መጽሐፍ የተተረጎመ

ኮሮናቫይረስ እና ክርስቶስ
የዐማርኛ ትርጉም ግንቦት 2012 ዓ.ም.

የባለቤትነት ሕጋዊ መብት (ኮፒራይት) ©2020 በዲዛየሪንግ ጋድ ፋውንዴሽን

አሳታሚ፡- ክሮስዌይ
Crossway
1300 Crescent Street
Wheaton, Illinois 60187

የአሳታሚው መብት በህግ የተጠበቀ ነው። በቅድሚያ በጽሑፍ የተረጋገጠ ሕጋዊ ፈቃድ ሳያገኙ የዚህን መጽሐፍ ማንኛውንም ክፍል ማባዛት፣ ማተም፣ በዲጂታል (ሶፍት ኮፒ) መገልበጥ፣ በዲጂታል (በሶፍት ኮፒ) የተዘጋጀውን በማንኛውም መንገድ፣ በኤሌክትሮኒክ፣ በፎቶኮፒ፣ በድምጽ በመቅረጽ፣ ወይም በሌላ እዚህ ባልተጠቀሰ መንገድ ማባዛት በህግ የተከለከለ ነው።

በቀጥታ ካልተጠቀሰ በስተቀር፣ ለዚህ ትርጉም የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች የተወሰዱት በ1993 ዓ.ም. በቢብሊካ ከታተመው ዐዲሱ መደበኛ ትርጉም መጽሐፍ ቅዱስ ነው።

ይህ ኮሮናቫይረስ እና ክርስቶስ መጽሐፍ በዲዛየሪንግ ጋድ ፋውንዴሽን ፈቃድ፣ ለሶፍት ኮፒ ነጻ ሥርጭት ብቻ እንዲውል በገርጂ አማኑኤል ኅብረት ቤተ ክርስቲያን ወደ ዐማርኛ የተተረጎመ ነው።

ትርጉም፡- ኤርሚያስ ሰብስቤ | አርትዖት፡- ፍጹም ግርማ፣ ዲያቆን አግዛቸው ተፈራ

ተጨማሪ አርትዖት፣ ማሻሻያ እና ጠቅላላ የሕትመት ዝግጅት፡-
ስፕሬድ ኦፍ ግሬስ ሚኒስትሪስ (Spread of Grace Ministries, USA)

GEUC
GERJI EMMANUEL UNITED CHURCH
GENERATION EQUIPING UNDER CHRIST
ገርጂ አማኑኤል ኅብረት ቤተ ክርስቲያን

ገርጂ አማኑኤል ኅብረት ቤተ ክርስቲያን ትውልድን በእግዚአብሔር ፈቃድ፣ ከክርስቶስ ስር፣ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ለማስታጠቅ የምትሠራ፣ ይህንንም በትምህርት፣ በጸሎት፣ በኅብረት፣ በአምልኮ እና በአገልግሎት የምትተገብር በአዲስ አበባ ገርጂ አከባቢ የምትገኝ አጥቢያ ናት።

desiringGod
desiringGod.org

ማውጫ

ወቅቱ፡- ኮሮናቫይረስ 9

ክፍል 1፡- ከኮሮናቫይረስ በላይ የሆነው እግዚአብሔር

1. ኑ ወደ ዐለቱ 13
2. ጽኑ መሠረት 23
3. ዐለቱ ጻድቅ ነው 31
4. በኹሉ ላይ ሉዓላዊ 39
5. የአገዛዙ ምቹነት 47

ክፍል 2፡- እግዚአብሔር በኮሮናቫይረስ ምን እየሠራ ነው?

ቀዳሚ ሐሳብ፡- ማየትና ማመልከት 57

6. ግብረገባዊ ክፋትን ማሳየት 63
7. ተገቢ መለኮታዊ ፍርድን መላክ 71
8. ለዳግም ምጽአት እያነቃን 75
9. በእውነተኛ ንስሓ ራሳችንን ያለገደብ ለክርስቶስ መስጠት 79
10. በአደጋ ውስጥ መልካም ሥራዎችን መፍጠር 89
11. ሕዝብን ለመድረስ ሥርን ማላላት 97

የማጠቃለያ ጸሎት 101

ማስታወሻ 103

ዋቢ መጻህፍት (ማጣቀሻ) 103

በዲዛየሪንግ ጋድ (እግዚአብሔርን መፈለግ) አገልግሎት
ተዘጋጅተው ስለቀረቡ ትምህርቶች 105

ወቅቱ፡-

ኮሮናቫይረስ

ይህን ትንሽ መጽሐፍ እየጻፍሁኝ ያለሁት ምድራችን “የኮሮና ቫይረስ በሽታ 2019” (በምጎጻረ ቃል አጠራሩ ኮቪድ-19) በተሰኘ ዓለም ዐቀፍ ወረርሽኝ እየታመሰች ባለበት የወርኅ መጋቢት 2020 የመጨረሻ ቀናት ላይ ሆኜ ነው። ይህ ጎጂ ሕዋስ (ቫይረስ) የመተንፈሻ አካላትን የሚያጠቃ ሲሆን፣ ከረር ሲልም ትንፋሽ በማሳጠር ለኅልፈተ ሕይወት ያበቃል።

በቫይረሱ ጥቃት የመጀመሪያው ሞት ዘገባ የተሰማው ከወደ ቻይና በጥር 11 ቀን 2020 ዓ.ም ነበር። ይህን ጽሑፍ በምጽፍበት ወቅት በቫይረሱ የተጠቁ ሰዎች ቍጥር በመቶ ሺሕዎች፣ ሟቾች ደግሞ በዐሥር ሺሕዎች የሚቈጠሩ ሆነዋል። እስከ አሁን ድረስም ፈውስ አልተገኘለትም።

ይህን በምታነቡበት ወቅት ደግሞ ችግሩ ምን ደረጃ ላይ እንደደረሰ ከእኔ በተሻለ ሁኔታ ልታውቁ ትችላላችሁ። (ይህ መጽሐፉ በአማርኛ ተተርጉሞ ለአንባቢያን እየተዘጋጀ ባለበት ሰአት በበሽታው የተያዙ ሰዎች ቁጥር ከአራት ተኩል ሚሊዮን በላይ የደረሰ ሲሆን፣ የሟቾች

ቁጥር ደግሞ ከሦስት መቶ ሺህ በላይ ደርሷል።) ስለዚህ የቫይረሱን ሥርጭት ለመግታት እየተወሰዱ ስላሉ ርምጃዎች ወይም በኢኮኖሚ ላይ እየደረሰ ስላለው ጫና እና ቀውስ መዘርዘር አያስፈልገኝም። ማኅበራዊ መርሐ ግብሮች፣ ጉዞዎች፣ ስብሰባዎች፣ የቤተ እምነት ስብሰባዎች፣ ሲኒማና ቴአትር ቤቶች፣ ምግብ ቤቶች፣ ስፖርታዊ ክንውኖች፣ እንዲሁም የንግድ ስፍራዎች ለመዘጋት በቋፍ ላይ ናቸው።

ይህ በአሜሪካም ሆነ በዓለም ዐቀፍ ደረጃ ታይቶ የማይታወቅ ነገር አይደለም። በ1918 ዓ.ም.ቱ የኢንፍሉዌንዛ ወረርሽኝ (የጎዳር በሽታ)፣ እንደ በሽታ ቍጥጥር ማእከል (Centers for Disease Control) ግምት ከሆነ ከመላው ዓለም ወደ ኀምሳ ሚሊዮን የሚጠጉ ሰዎች ሕይወ ታቸውን ዐጥተዋል።[1] ከሚኾች ውስጥም ዐምስት መቶ ሺሕ የሚያ ህሉት አሜሪካውያን ነበሩ። ጠዋት ላይ የሕመሙ ምልክት የታየባቸው ሰዎች እኩለ ሌሊት ላይ ሕይወታቸው ዐልፏል። አስክሬኖች ከየበረን ዳው እየተሰበሰቡ በጋሪ ተጭነው ወደ ጅምላ መቃብሮች ተጉዘዋል። የፊት መሸፈኛ ጭንብል አላደረግህም ተብሎ ሰው በጥይት ተገድሏል። ትምህርት ቤቶች ተዘግተው ነበር። መንፈሳዊ አገልጋዮች ስለ አርማጌ ዶን ተናግረውም ነበር።

በርግጥ ከዚህ ቀደም ታይቶ መታወቁ ምንም አያረጋግጥም። ያለፈው ማስጠንቀቂያ እንጂ መደምደሚያ ዕጣ ፈንታ አይደለም። የሆነው ሆኖ ይህ ጊዜ የዚህችን ዓለም ስርአት መፈረካከስ በተጨባጭ እየታየ ያለበት ወቅት ነው። ጠንካራ የሚመስሉ መሠረቶች ሲናወጡ እያየን ነው። ልንጠይቀው የሚገባ ጥያቄ፣ እግራችን የቆመበት ዐለት አለን ወይ? የሚል ነው። ለዘላለም የማይናወጥ ዐለት?

ክፍል 1

በኮሮናቫይረስ ላይ ገዢ የሆነው እግዚአብሔር

ምዕራፍ 1

ኑ ወደ ዐለቱ

ይህን መጽሐፍ ለመጻፍ ያነሣሣኝ በሞላ ጎደለ (የእድል ጨዋታ) ወይንም በእድል ላይ ብቻ የመኖር ተስፋችንን ማድረግ ተሰባሪና ተንኮ ታኳች ስለሆነ ነው። ሞላ ጎደለ ስል ሦስት ከመቶ ወይም አሥር ከመቶ ዕድል፣ ወጣት ከአዛውንት፣ ተጓዳኝ ሕመም ያለባቸው ከሌለባቸው፣ በገጠር የሚኖረው በከተማ ከሚኖረው፣ ራስን ለይቶ ያቆየው ቤቱ ከወዳጆቹ ጋር ከሚሰባሰበው ጋር እየተወዳደረ የሚኖረውን የመትረፍ ዕድል ነው። ይህ በሞላ ጎደለ ላይ የተደገፈ ሕይወት ትንሽ ተስፋ ይኖረው ይሆናል፤ ነገር ግን ተማምነን የምንቆምበት የጸና ስፍራ አይደለም።

ሌላ የተሻለ መንገድ አለ። ለመቆም ሌላ የተሻለ ስፍራ አለ። ከዕድ ሎች አሸዋ ይልቅ የምንተማመንበት የዐለት መሠረት።

የካንሰር ሕመም ሰሞን

በታኅሣሥ 21 ቀን 2005 የፕሮስቴት ካንሰር እንደ ነበረብኝ ተነግሮኝ ነበር። ከዚያ ቀን በኋላ ባሉ ተከታታይ ሳምንታት ወሬው ሁሉ ስለ ዕድሎች ሆነ። የሚሆነውን ዝም ብሎ በማየት ውስጥ ያለ ዕድል። መድኀኒቶችን በመጠቀም ውስጥ ስላለው ዕድል። ሆሚዮፓቲክ ሂደቶችን በመከተል ውስጥ ስላለው ዕድል። (ሆሚዮፓቲክ የሰው አካል በተፈጥሮአዊ መንገድ ከታገዘ በራሱ በሽታን የመዋጋት አቅም እንዳለው በመንገዘብ ላይ የተመረኮዘ የህክምና አማራጭ ነው)። ሙሉ ቀዶ ጥገና በማድረግ ውስጥ ስላለው ዕድል። ባለቤቴ ኖኤል እና እኔ እነዚህን ዕድሎች በሥርዐት ነበር የምናስባቸው። ነገር ግን ሲመሽ እርስ በእርሳችን እንሣሣቅና ይህን እናስባለን፡- *ተሰፋችን ዕድሎቹ ውስጥ ሓይደለም። ተሰፋችን በእግዚአብሔር ነው።*

ይህን ስንል “መቶ በመቶ እግዚአብሔር ያድነኛል፣ ሐኪሞች የዕድል ሙከራ ብቻ ነው የሚሰጡኝ” እያልሁ አልነበረም። እያወራሁለት ያለው ዐለት ከዚህ የተሻለ ነው። አዎን፣ ከፈውስ የተሻለ ዐለት።

ካንሰር እንዳለብኝ ከነገረኝ ዶክተር የስልክ ጥሪ በፊት እግዚአብሔር በሚደንቅ መንገድ እግሮቼ ስለ ቆሙበት ዐለት አስታውሶኝ ነበር። ከተለመደው ዓመታዊው የሕክምና ምርመራዬ በኋላ፣ ዶክተሩ አየኝና፡-

“ባዮፕሲ (የላቦራቶሪ ምርመራ ዐይነት ነው) መሥራት እፈልጋለሁ” አለኝ።

በእርግጥ ትፈልጋለህ ነው? ብዬ አሰብ አደረኩ። “መቼ?”

“ጊዜ ካለህ፣ አሁን።”

“ይኖረኛል።” አልኩት።

ይህን ብሎኝ የመመርመሪያ መሣሪያውን ሊያስተካክል ሲሄድና እኔም ልብሴን ወደ ሰማያዊ የሀኪም ቤት ልብስ (ጋዎን) ስቀይር ምን እየተፈጠረ እንዳለ እንዳሰላስል በቂ ጊዜ አግኝቼ ነበር። ለራሴ "ሐኪሙ ካንሰር ሊኖርብኝ እንደሚችል እያሰበ ነው ማለት ነው" አልሁ። በዚህም ምክንያት በዚህች ዓለም ያለኝ የወደፊት ሕይወት ሲቀየር በዐይነ ኅሊናዬ እየታሰበኝ፣ በቅርብ ያነበብሁትን አንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል እግዚአብሔር ወደ አእምሮዬ አመጣ።

እግዚአብሔር ተናገረ

እዚህ ላይ አንድን ነገር ግልጽ ማድረግ ይኖርብኛል። የተለየ መንፈሳዊ ድምፅ የመስማት ልምድ የለኝም። ቢያንስ እስከ ዛሬ ሰምቼ አላውቅም። እግዚአብሔር እንደሚናገር ርግጠኛ የምሆነው መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል እንደ ሆነ ስለማምን ነው። አንዴ ለሁሉም ተናግሯል። በቃሉ አሁንም ይናገራል። መጽሐፍ ቅዱስን በትክክል ለተረዳው የእግዚአብሔር ድምፅ ነው።

ካንሰር እንዳለብኝና እንደሌለብኝ የሚያረጋግጠውን የባዮፕሲ ምርመራ ለማድረግ በዶክተሩ ቢሮ ውስጥ ሆኜ እየተጠባበቅሁኝ እግዚአብሔር ይህን ተናገረኝ፦ "ጆን ፓይፐር፣ ይህ ቀላል አይደለም። ብትኖር ወይም ብትሞት ከኔ ጋር ትሆናለህ።" በርግጥ ይህ እኔ በራሴ መንገድ አጠር አድርጌ የገለጽኩት አገላለጽ ነው፤ እርሱ ቃል በቃል እንዲህ ነበር ያለኝ፦

“እግዚአብሔር ድነትን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ አማካይ ነት እንድናገኝ ነው እንጂ ለቀጣ ወስኖ አላስቀመጠንምና። ብንነቃም ሆነ ብናንቀላፋ ከእርሱ ጋር በሕይወት እንድ ንኖር እርሱ ስለ እኛ ሞተ። (1ተሰ. 5፥9-10)

ብነቃም ባንቀላፋም …ብኖርም ብሞትም …ከእግዚአብሔር ጋር በሕይወት እኖራለሁ። ግን ለኔ ለጎጢአተኛው ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል? አንድም ቀን እግዚአብሔር የሚፈልገውን አይነት የቅድስናና የፍቅር ደረጃ ኖሬ የማላውቀውን እኔን እርሱ እግዚአብሔር እንዴት “አንተ ጆን ፓይፐር ብትኖርም ብትሞትም ከእኔ ጋር ትሆናለህ” ሊለኝ ይችላል?

ይህ ሊሆን የቻለው ከክርስቶስ የተነሣ ነው። በክርስቶስ ብቻ። ከእርሱ ሞት የተነሣ ምንም ዐይነት ቀጣ በእኔ ላይ አይሆንም። እኔ ፍጹም ሆኜ አይደለም። የኔ ኃጢአት፣ የኔ ጥፋት፣ የኔ ቅጣት ሁሉ በአዳኜ በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ሆኗልና። ቃሉ እንደሚለው እርሱ ስለ እኛ ሞቷል። ስለዚህ እኔ ከጥፋተኛነት ነጻ ነኝ። ከቅጣትም ነጻ ነኝ። በእግዚአብሔር ምሕረት የተጠበቅሁ ነኝ። ብሞትም ብኖርም፣ እግዚ አብሔር የሚለኝ “ከእኔ ጋር ትኖራለህ” ነው።

ይህ በካንሰር ምክንያት ከገጠሙኝ ዕድሎች ጋር ከመጫወት በጣም ይለያል። ከኮሮናቫይረስ ዕድሎችም እንዲሁ። ይህ እግሮቼ የቆሙበት የጸናው ዐለት ነው። የማይሰበር ደግሞም አሸዋ ያልሆነ። በዚህ ዐለት ላይ የእናንተም እግሮች ይቆሙ ዘንድ እወዳለሁ። ይህን የምጽፈውም በዚሁ ምክንያት ነው።

ይህ ዐለት የሚጠቅመው ከመቃብር ወዲያ ብቻ ነውን?

በፍጹም። ይህን የሚያነብ አንድ ሰው እንዲህ ሊል ይችላል፡- “እንደ አንተ ያለ ሃይማኖተኛ ሰው ተስፋን የሚሰጠው ከፍጻሜ በኋላ ስላለ ዓለም ነው። ከመቃብር በኋላ ስላለ ድነት ብቻ። የምታወሩለት የእግዚአብሔር ድምፅ አሁን እየሆነ ስላለው ነገር ብዙም ግድ አይለ ውም። እግዚአብሔር ነገሮችን በፍጥረት እንደ ጀመረ ደግሞም በሚደንቅ መደምደሚያ ሁሉን አንደሚጠቀልል ይነገራል። ነገር ግን በመካከል እየሆነ ላለው ነገርስ? አሁን እግዚአብሔር የት ነው ያለው? በዚህ በኮሮናቫይረስ ወረርሽኝ ወቅትስ?”

እንግዲህ እኔ በሕይወቴ ትልቁን ዋጋ የምሰጠው መጨረሻ በሌለ ውና በእግዚአብሔር መገኘት ውስጥ ስለሚሆን ገደብ የለሽ የዘላለም ሕይወት ነው። ሆኖም ግን እግሮቼ የቆሙበት ዐለት *ኣሁንም* ቢሆን እንደ ቆምሁበት ነው። *ኣሁንም!*

እርግጥ ነው የምኖረው ኮሮናቫይረስ ባለበት ዓለም ውስጥ ነው። ምናልባት ኮሮናቫይረስ ባይገድለኝ ካንሰሩ በድጋሚ አገርሽቶ ወይም ደግሞ በ2014 ገጥሞኝ የነበረው የሳንባ የደም ቧንቧ መዘጋት በእንግሊ ዝኛው (አንፐሮቮክድ ፕልመናሪ ኤምቦሊዝም) የሚባለው ወደ አእም ሮዬ ወጥቶ ቢሆን ኖሮ በድጋሚ አንድም ዐረፍተ ነገር መጻፍ የማልችል አድርጎኝ ሊያልፍ ይችል ነበር። አለዚያም ያላስተዋልናቸው እጅግ ብዙ አደጋዎች እኔንም እናንተንም በየትኛውም ጊዜ ሊወስዱን ይችላሉ።

እየተናገርሁለት ያለውና የጸናው ዐለት *ኣሁንም* እግሮቼ እንደ ቆሙበት ነው ስል ከሞት ባሻገር ያለው ተስፋ *የኣሁንም ጭምር* ስለሆነ

ነው። የተስፋ ፍጻሜ ወደፊት ነው፤ የተስፋ ልምምድ ግን የአሁን ነው። ይህ የአሁን ጊዜ ልምምድ ደግሞ ጎይለኛ ነው።

ተስፋ ጎይል ነው። የአሁን ጎይል። ተስፋ ሰዎች ራሳቸውን ከማጥ ፋት ይታደጋቸዋል — አሁን። ተስፋ ሰዎች በማለዳ ከእንቅልፋቸው ነቅተው ወደ ሥራቸው እንዲሄዱ ያደርጋቸዋል — አሁን። ተስፋ ለሰዎች የየዕለት ሕይወት ትርጉም ይሰጣል፤ በቀሳ[1]ም (በለይቶ ማቈያም) ሆነ በቤት ውስጥ በመቈየት ጊዜ — አሁን። ተስፋ ፍቅርን ያነሣሣል፤ መሥዋ ዕትነትን ያስከፍላል - አሁን።

ስለዚህ ከመቃብር ባሻገር ያለውን ተስፋ እንዳናቃልል ልንጠነ ቀቅ ይገባል። ምክንያቱም ፍጻሜያችን ያማረና የተረጋገጠ ሲሆን፣ አሁናችንና እዚያችን ጣፋጭና ፍሬያማ ይሆናል።

የእርሱ ጣት በቫይረሶች ላይ

በዶክተሩ ቢሮ ውስጥ እያለሁ ለእነዚያ እግዚአብሔር ለተናገረኝ ጣፋጭ ቃሎች መመለስ የቻልሁት ነገር ቢኖር "ብኖርም ብሞትም፣ አንተ ከኔ ጋር ትኖራለህ" የሚል ነበር። በክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ ያገኘሁት ተስፋ ለሌሎች ጥቅም እንዲሆን ለሥጋ እኖረው ዘንድ እወዳለሁ...በተለይ ለዘላለማዊ ጥቅማቸው። ይህ ተስፋ ሕይወቴን ላለማባከን ጥልቅ ፍላጎት ያሳድርብኛል። የኢየሱስ ክርስቶስን ታላቅነት ለማሳወቅ በቅንአት ይሞላኛል። የቻልሁትን ያክል ገንዘቤንም ራሴንም

[1] "ቀሳ፣ ብቻ ብቻነት ልዩነት። ፈረንጆች ኳራንቲን ከሚሉት ጋር ይስማማል።" (ደስታ ተክለ ወልድ፣ ዐዲስ ያማርኛ መዝገበ ቃላት፣ ገጽ 1626፻198)።

እየከፈልሁ (2ቆሮ. 12፥15) ብዙ ሰዎች ከእኔ ጋር ወደ ዘላለማዊ ደስታ አመጣ ዘንድ ያነሣሣኛል።

ምንም እንኳ ማለት የምችለው ይህን ቢሆንም፣ “የፓይፐር እግዚአብሔር የሚያተኩረው ከመቃብር ባሻገር ባለው ነገር ላይ ብቻ ነው፤ ስለ አሁኑኑ አይደለም” የሚል ተቃውሞ ቢነሣ፣ መልሱ ይህ ብቻ አይደለም የሚል ነው።

አሁን ልናገረው ያለው ነገር የቅድሙን ተቃውሞ ያነሣ የነበረውን “አ! ይህማ እግዚአብሔርን በአሁንና በእዚህ (በምድር) ጉዳዮች በጣም የበዛ ተሳትፎ እንዲኖረው ያደርጋል። አሁን ከመቃብር ባሻገር ያለውን ህይወት ከሚያሳምር አምላክ፣ በቫይረሶች ውስጥ ጣቱን ወደሚያስገባ አምላክ መጣህ” ያሰኘዋል።

“ደኅና ነኝ ” ሳይሆን “ደኅና እንደ ሆንሁኝ ይሰማኛል”

የካንሰር ምርመራ ከማድረጌ በፊት ሰዎች ደኅንነቴን ሲጠይቁኝ መልሴ ደኅና ነኝ የሚል ነበር። ከዚያ በኋላ ግን እንደዚያ መመለስ አቁሜአለሁ። ይልቅስ ደኅና እንደ ሆንሁ ይሰማኛል እላለሁ። በሁለቱ መካከል ልዩነት አለ። ለመደበኛ የሕክምና ምርመራ ወደ ሆስፒታል ከመሄዴ አንድ ቀን በፊት ደኅና እንደ ሆንሁኝ ዐስብ ነበር። ከአንድ ቀን በኋላ ግን ካንሰር እንዳለብኝ ተነገረኝ። በሌላ ቋንቋ ደኅና አልነበርሁም ማለት ነው። ይህን ስጽፍ ራሱ ደኅና መሆኔን አላውቅም። ነገር ግን ከሚገባኝ በላይ ደኅና እንደ ሆንሁ ይሰማኛል። የማውቀው ነገር የካንሰር ታማሚ እንደ ሆንሁ ነው። ምናልባትም የደም መርጋት ሊኖርብኝም ይችላል ወይም ኮሮናቫይረስ።

ምንድነው እያልሁ ያለሁት? “ደኅና ነኝ” እንዳንል የሚያግደን ምክንያት ደኅና መሆናችንን የሚያውቅና የሚወስን እርሱ እግዚአብሔር ብቻ በመሆኑ ነው – አሁን። ደኅና መሆናችንን ሳናውቅና ደኅንነታችንን በፈቃዳችን መቈጣጠር ሳንችል ደኅና ነኝ ማለት፣ ነገ በሕይወት መኖራ ችንን ሳናውቅ “ነገ ወደ ቺካጎ እሄዳለሁ፤ በዚያም እነግድና አተርፋለሁ” እንደ ማለት ነው። ስለዚህ ጕዳይ መጽሐፍ ቅዱስ የሚለን፦

> “እናንተ ‘ዛሬ ወይም ነገ ወደዚህች ወይም ወደዚያች ከተማ እንሄዳለን፤ በእርሷም አንድ ዓመት እንቈያለን፤ እንነግዳለን፤ እናተርፋለንም’ የምትሉ እንግዲህ ስሙ። ነገ የሚሆነውን እንኳ አታውቁም። ሕይወታችሁ ምንድን ናት? ለጥቂት ጊዜ ታይቶ ኀላ እንደሚጠፋ እንፋሎት ናችሁ። ይልቁንም፣ “የጌታ ፈቃድ ቢሆን እንኖራለን፤ ይህን ወይም ያንን እናደርጋለን” ማለት ይገባችኋል።” (ያዕ. 4፥13-15)

አሁን ደግሞ እንደ እንፋሎት በሆነው ጊዜያዊ ዕውቀታችን ላይ መጽሐፍ ቅዱሳዊውን የእውነት ብርሃን ስንገልጥበት ከመቃብር ባሻገር ባለው ሕይወት ብቻ ይሳተፋል ያልነው እግዚአብሔር ወደ *ለሁን* ጊዜ መጣ።

እርሱ ቢፈቅድ ብንኖርም ይህን ወይም ያንን እናደርጋለን

እግሮቼ የቆሙበትና የእናንተም እግሮች እንዲቆሙበት የምመ ኘው ይህ ዐለት *በለሁን* እና *በዘላለም* ውስጥ ጸንቶ የሚኖር የእግዚ አብሔር ዐለት ነው። “የጌታ ፈቃድ ቢሆን” መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚል

“እንኖራለን”። ይህም የእግዚአብሔርን የአሁን ዘመን ግልጽ ተሳትፎ ያሳያል። ብትሞት ወይም ብትኖር ከእርሱ ጋር ትኖራለህ ብቻ ሳይሆን እግዚአብሔር እንድትኖር ወይም እንድትሞት ይወስናል - ለሁን።

ደግሞም ስለ መሞትና ስለ መኖር ብቻ ሳይሆን “የጌታ ፍቃድ ቢሆን”...“ይህን ወይም ያን እናደርጋለን”። “ይህን ወይም ያን” በሚለው አባባል ውስጥ የማይካተት አንድም ነገር አይኖርም። እርሱ በነገሮቻችን ሁሉ ሙሉ በሙሉ ይሳተፋል። ሙሉ በሙሉ። በዚህ ጤንነት ወይም በዚያ ሕመም። በዚህ የኢኮኖሚ ውድቀት ወይም በዚያ ማንሰራራት። በዚህ እስትንፋሳችን ወይም በዚያ መተንፈስ አለመቻላችን።

በዚያ ዶክተር ቢሮ ውስጥ ሆኜ የባዮፕሲ መሣሪያ እስኪመጣ ድረስ ስጠብቅ እግዚአብሔር ያለኝ ነገር፦ “አትፍራ። ብትኖር ወይንም ብትሞት ከእኔ ጋር ትኖራለህ። ብትኖር እንዲሆንብህ ያልፈቀድሁት አንዳች ነገር በሕይወትህ አይፈጠርም። በሕይወት እንድትኖር ከፈቀድሁ በሕይወት ትኖራለህ። እንድትሞት ከፈቀድሁ ደግሞ ትሞታለህ። በኔ ፈቃድ እስክትሞት ደግሞ እንድታደርግ የፈቀድሁትን ይህን ወይም ያን ታደርጋለህ።”

የኔ ዐለት ይህ ነው — ለዛሬ፣ ለነገ ብሎም ለዘላለም።

ወደ ዐለቱ ኑ

ይህ መጽሐፍ ወደ ጸናው ዐለት ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ መጥታችሁ ትቀላቀሉኝ ዘንድ ያቀረብኩላችሁ ግብዣ ነው። መጽሐፉን ማንበብ ስትቀጥሉ ምን እያልኋችሁ እንደ ሆነ ግልጽ እየሆነ እንደሚመጣ ተስፋ

አደርጋለሁ። ዐላማዬ የታሪክ ክሥተት በሆነው በኮሮናቫይረስ ወረርሽኝ ውስጥ እግዚአብሔር በክርስቶስ ሆኖ የጸና ዐለት መሆኑንና በእርሱ ጎያል ፍቅር ላይ መቆም ምን እንደሚመስል ማሳየት ነው።

ምዕራፍ 2

ጽኑ መሠረት

ስለ ኮሮናቫይረስም ሆነ ስለ ሌላ ማንኛውም ነገር የእኔ አሳብ ብዙ ፋይዳ ላይኖረው ይችላል። እግዚአብሔር የሚያስበውና የሚናገረው ግን ፋይዳው ለአሁን ብቻ ሳይሆን ለዘላለም ነው። እርሱም ታዲያ፣ ስለሚያስበው ነገር ዝም ብሎ አያውቅም። ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎ ችም ስለዚህ ከሥተት የሚሉት ነገር አላቸው።

ጽኑና ጣፋጭ

የኔ ድምፅ እንደ ሣር ጊዜያዊ ነው፤ የእግዚአብሔር ድምፅ ግን እንደ ግራናይት(የእምነበረድ አይነት ሆኖ የተለያየ ቀለም ያለው ዐለት ነው) ዐለት የጸና ነው። “ሣሩ ይጠወልጋል፤ አበባውም ይረግፋል፤ የጌታ ቃል ግን ለዘላለም ጸንቶ ይኖራል።” (1ጴጥ. 1፥24-25) እንዲል ቃሉ። ኢየሱስ በመጽሐፍ ያለው የእግዚአብሔር ቃል ሊሻር የማይችል እንደ

ሆነ ተናግሯል (ዮሐ. 10፥35)። እግዚአብሔር የሚናገረውም እውነትና ጽድቅን በአንድነት ነው (መዝ. 19፥9)። ስለዚህ የእግዚአብሔር ቃል ለሕይወት የጸና መሠረት ነው። ምስክርነቱም ከጥንት ጀምሮ የመሠረታቸው ናቸው (መዝ. 119፥152)። እግዚአብሔርን መስማትና እርሱን ማመን ደግሞ ቤትን በአሸዋ ላይ ሳይሆን በዐለት ላይ እንደ መገንባት ነው (ማቴ. 7፥24)።

እርሱ በቃሉ ሲመክር ቀልብን ሰብስበውና ልብ ብለው የሚያዳም ጡት ዐይነት ነው። “በምክሩ ድንቅ በጥበቡ ታላቅ ነው” (ኢሳ. 28፥29)። “ለጥበቡም ወሰን የለውም” (መዝ. 147፥5)። ስለ ኮሮናም ሲመክር ምክሩ የጸና፣ የማይናወጥና የዘላለም ነው። “የእግዚአብሔር ሐሳብ ግን ለዘላለም ይጸናል” (መዝ. 33፥11)። ደግሞም “የአምላክ መንገዱ ፍጹም ነው” (2ሳሙ. 22፥31)።

ስለዚህም የእግዚአብሔር ቃል ጣፋጭ ደግሞም እጅግ የከበረ ነው። “ከወርቅ ይልቅ የከበረ፣ እጅግ ከጠራ ወርቅም የተሻለ ነው፤ ከማር ይልቅ ይጣፍጣል፤ ከማር ወለላም ይበልጥ ይጥማል።” (መዝ. 19፥10)። በርግጥም የእግዚአብሔር ቃል የዘላለም ሕይወት ጣፋጭ ጣዕም ነው፦ “ጌታ ሆይ፤ ወደ ማን እንሄዳለን? አንተ የዘላለም ሕይወት ቃል አለህ (ዮሐ. 6፥68)።”

ስለዚህ በሚመቹም ሆነ በማይመቹ ጊዜያት የእግዚአብሔር ቃል የማይናወጥ ሰላምና ደስታን ያጐናጽፋል። ይህን መጽሐፍ የሚያነብቡ

ሁሉ ነቢዩ ኤርምያስ “ቃልህ ሐሤትና የልብ ደስታ ሆነልኝ።” (ኤር. 15፥16) ያለበትን ልምድ ይካፈሉ ዘንድ ጸሎቴ ነው።

ይህን ልብ በሉ፦ የእግዚአብሔር ቃል አሁን እንዳለንበት ዐይነት መራራ መግቦቱ ውስጥም ቢሆን ጣፋጭነቱን እንደማያጣ ልናስተውል ይገባል። ደግሞም “ሐዘንተኞች ስንሆን ሁል ጊዜ ደስተኞች ነን።” (2ቆሮ. 6፥10) የሚለውን ቃል ምስጢር ልንረዳ ይገባል። ይህን ምስ ጢር ወደ ፊት በደንብ የምናየው ቢሆንም አሁን በአንድ ዐረፍተ ነገር እንዲህ ይገለጣል፦ “*የኮሮናቫይረስ ወረርሽኝን ማሰቆም የሚችል ሉዓላ ዊነት፣ ግን ያላሰቆመ፤ ያው ሉዓላዊነት፣ በዚያው ወረርሺኝ ውስጥ ሕይወትን የሚያስቀጥልና የሚደግፍ ነው።*” የሚለውን መረዳት ነው። በርግጥ ከመደገፍም ባለፈ ሕይወትን ያጣፍጣል። እርሱን አምነውት ለሚሞቱ እንኳ የእግዚአብሔር ሐሳብ ፍጹም መልካም መሆኑን በሚያ ስረዳ ተስፋ ያጣፍጠዋል።

እንዴት ልታውቅ ቻልህ?

መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል መሆኑን እንዴት ልታውቅ ቻልህ? የሚል ጥያቄ ቢኖር ያለኝ ዐጭር መልስ የሚከተለውን ይመስ ላል። “በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በሚያበራው መለኮታዊ ክብር በኩል እግዚአብሔር ብቻ ሊሞላው የሚችለውን የልባችንን ክፍተት በትክክል ስለሚሞላው።” ልክ እንደ እጅና ጓንት፣ እንደ ጥርስና ማርሽ፣ እንደ ዓሣና ውሃ፣ አሊያም እንደ ክንፍና የሚያንሳፍፈው አየር።

“ይህ የማይዳሰስ ረቂቅና ግላዊ መልስ ነው። ለምን እንዲህ ዐይነት መልስ መስጠት አስፈለገ?” የሚል ጥያቄ ሊኖር እንደሚችል እገምታለሁ።

ምክንያቱ፣ ከጎምሳ ዓመት በፊት ሕይወቴን ምን ላይ መመሥረት እንዳለብኝ ለማወቅ ስጣጣር፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪካዊና ምሁራዊ ትንታኔዎች አብዛኛውን የዓለም ሕዝብ ላያግዙ እንደሚችሉ ተረዳሁ። ምክንያቱም ታሪካዊና ምሁራዊ ትንተናዎች ጥሩና ዐጋዥ ቢሆኑም አንድን የስምንት ዓመት ልጅ እንኳ አይማርኩም። አለዚያም አንድ ያልተማረ፣ በገጠር ነዋሪ የሆነን ሰው እንዲረዳ ለማድረግ አይችሉም። ወይም ደግሞ በቀለም ትምህርቱ እምብዛም ያልዘለቀን ሰው ትኩረት ሊገዙ አይችሉም። እግዚአብሔር ግን እንደዚህ ያሉ ሰዎች ቃሉን ይሰ ሙና ያምኑት ዘንድ እንደሚሻ እየተገለጠልኝ መጣ። እርሱን በመስማ ታቸውና በማመናቸው የሚመጣውን ውጤት ግን በርግጠኛነት ሳያው ቁት በጥርጣሬ እንዲከተሉት አይደለም።

መጽሐፍ ቅዱሳዊ እምነት የእውር ድንብር (የጭፍን) ጉዞ አይደለም

መጽሐፍ ቅዱሳዊው የእምነት ግንዛቤ ወይም እይታ፣ እንዲያው በይሆናልና በግምት ጨለማ ውስጥ ዘሎ የመግባት ዓይነት ነገር አይ ደለም። *እምነት* የተባለው መሠረት ስለሌለው አይደለም። *እምነት* የተባለው መተማመኛ፣ ዋስትና ስላለው ነው። ኢየሱስም፣ አማኞችን ሳይሆን የማያምኑትን ነበር ‘ዕውሮች’ ብሎ የጠራቸው (ማቴ. 15፥ 14)። በሌላ ስፍራም ‘እያዩ ስለማያዩ’ (ማቴ. 13፥13) ሲል እናያለን።

እንደ እግዚአብሔር ቃል የሆነና የሚያድነው እምነት የሚጀምረው ከማየት ነው።

ግን ምን ከማየት? መጽሐፍ ቅዱስ ሰይጣን ሰዎችን ለማሳወር አቅሙ የፈቀደውን ሁሉ እንደሚያደርግ ሲነግረን “የእግዚአብሔር አምሳል የሆነውን የክርስቶስ፣ የክብሩን ወንጌል ብርሃን እንዳያዩ፣ የዚህ ዓለም አምላክ የማያምኑትን ሰዎች ልቡና አሳውሮአል።” (2ቆሮ. 4፥4) ይለናል።

በሌላ አነጋገር በወንጌል በኩል የሚገለጥ መንፈሳዊ ብርሃን አለ - መጽሐፍ ቅዱሳዊ የድነት ታሪክ። “የእግዚአብሔር አምሳል የሆነውን የክርስቶስ የክብሩን ወንጌል ብርሃን” ነው። ይህ ምትሃታዊና እጅግ ምስጢራዊ ነገር አይደለም። ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም ሰውና ፍጹም አምላክ ሆኖ ግብረገባዊ (ሞራላዊ)፣ መንፈሳዊ ፣ እንዲሁም ልዕለ ተፈጥሮአዊ የሆነው ክብሩ እርሱም ታላቅነቱና ውበቱ፤ እንዲሁም ክብር የተገባው መሆኑ በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ያበራል። ይህም መጽሐፍ ቅዱስ እውነት እንደ ሆነ ያስረግጥልናል።

እግዚአብሔር ብቻ የሚሞላው የልባችን ክፍተት

ከመጽሐፍ ቅዱስ የሚገለጥ መለኮታዊ ክብር እግዚአብሔር ብቻ ሊሞላው የሚችለውን የልባችንን ክፍተት በትክክል ይሞላል ማለቴ ለዚህ ነበር። አዎን! እግዚአብሔር ብቻ ሊሞላው የሚችለው ክፍተት በልባችን እንዳለ አምናለሁ። ይህንም በሰው ሁሉ ዘንድ ያለ ቀጥተኛ ያልሆነ የእግዚአብሔር ዕውቀት ልንለው እንችላለን። መጽሐፍ ቅዱስ ስለዚህ ነገር ሲናገር “ስለ እግዚአብሔር ሊታወቅ የሚቻለው ለእነርሱ

ግልጽ ነው. . . እግዚአብሔርን ቢያውቁም እንኳ፣ እንደ አምላክነቱ አላከበሩትም” (ሮሜ 1፥19፡21) ይላል።

በሰው ሁሉ ዘንድ እንዲታወቅ በፍጥረት ላይ የተገለጸውን (አጠቃላይ መገለጥ ተብሎ የሚታወቀውን) የእግዚአብሔርን ክብር የማየት ኀላፊነት የኛ የሰዎች ነው። በተመሳሳይ መልኩ በቃሉ በኩል በግልጽ በክርስቶስ የተገለጠውን (ልዩ መገለጥ ተብሎ የሚታወቀውን) የእግዚአብሔርን ክብር የማየትም ኀላፊነት አለብን። ሰማያት የእግዚአብሔርን ክብር እንደሚናገሩ (መዝ. 19፥1) እኛም ክብሩን ልናይና ምስጋናን ለእግዚአብሔር ልንሰጥ እንደሚገባ፣ እንዲሁ የእግዚአብሔርም ልጅ የእግዚአብሔርን ክብር ገልጧል (ልዩ መገለጥ ተብሎ የሚታወቀው)፤ እኛም ይህን ልናስተውልና እግዚአብሔርንም ልናመልክ ይገባል። ሐዋርያው ዮሐንስ “ከአባቱ ዘንድ የመጣውን የአንድያ ልጅን ክብር አየን” (ዮሐ. 1፥14) ይላል።

ይህ እውነተኛነቱን ለራሱ የሚያረጋግጥበት፣ ከእግዚአብሔር ቃል የሚንጸባረቀው ክብሩ ሲሆን፣ ይኸውም ቅዱሳት መጻሕፍት ከእግዚአብሔር የተሰጡ እንደሆኑ ለማመን ጽኑ መሠረት ያለው እውነት ነው።

የቴክኖሎጂና የጣዕም ፍልሚያ

በመጽሐፍ ቅዱስ የተገለጠውን የእግዚአብሔር ክብር ወደ ማወቅ የምንመጣበት መንገድ ልክ ማር፣ ማር መሆኑን ቀምሰን ከምናውቅበት መንገድ ጋር ተመሳሳይነት ያለው ነው። ሳይንስና ቴክኖሎጂ በአንድ ጠርሙስ ውስጥ ያለን ነገር ትክክለኛ ማር እንደሆነ የሚያረጋግጡት ኬሚካላዊ የሆኑ ሙከራዎችን ካደረጉ በኋላ ሊሆን ይችላል። በተመሳ

ሳይ የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁራን መጽሐፍ ቅዱስ ከታሪክ አንጻር ያለውን እውነተኛነት በተመለከተ ሰፊ ማብራሪያ ያቀርቡም ይሆናል። የሚገር መው ግን አብዛኛው ሕዝብ ሳይንቲስት ወይንም ተመራማሪ አለመሆኑ ነው። ማር፣ ማር እንደ ሆነ ያወቅነው ቀምሰን ነው።

በተመሳሳይ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተገለጠው የእግዚአብሔር ክብር የራሱ የሆነ ጣዕም አለው። መዝሙረኛው “ቃልህ ለምላሴ ምንኛ ጣፋጭ ነው! ለአፌም ከማር ወለላ ይልቅ ጣዕም አለው።” (መዝ. 119፥103) ይላል። ደግሞም “እግዚአብሔር ቸር መሆኑን ቀምሳችሁ እዩ” (መዝ. 34፥8) ይላል። ይህ እውነተኛ ማየትና መቅመስ ነው—እውነት የሆነን ነገር ማየትና መቅመስ።

አሜን! የመጽናናታችን ዐለት ለሆነው የምንሰጠው ምላሽ

ኢየሱስ “መጻሕፍት ሊሻሩ አይችሉም” (ዮሐ. 10፥35) ሲል፣ ሐዋርያው ጳውሎስም “ቅዱሳት መጻሕፍት ሁሉ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለባቸው ናቸው” (2ጢሞ. 3፥16) ሲለን፣ ሐዋርያው ጴጥሮስ ደግሞ ቅዱሳት መጻሕፍትን ስለ ጻፉት ሰዎች ሲመሰክር “በመንፈስ ቅዱስ ተመርተው” (2ጴጥ. 1፥21) ሲል ልባችን *አሜን!* ይላል። ምክን ያቱም ቀምሰነዋል፤ ደግሞም አይተነዋል። ዐውቀነዋል። ዕውቀታችንም በጽኑ የተመሠረተ ነው። በጭፍን የምንጓዝ አይደለንም።

ስለዚህ ነፍሳችን “ቃልህ በሙሉ እውነት ነው” (መዝ. 119፥130) የሚለውን ስትሰማ፣ “እግዚአብሔር ሆይ ቃልህ በሰማይ፣ ለዘላ ለም ጸንቶ ይኖራል” (መዝ. 119፥89) የሚለውን ስታነብ፣ “የእግዚአ

ብሔር ቃል ሁሉ እንከን የለበትም” (ምሳ. 30፥5) ስትባል፣ ደግማ ደጋግማ ዐብራ በደስታ ትለዋለች። ሐሤትም ታደርጋለች።

ይህ የእግዚአብሔር እውነት በልባችን በፈሰሰ ጊዜ፣ በዚህ በኮሮና ቫይረስ ወቅት እንኳ ቢሆን ተወዳዳሪ የሌለው መጽናናት ያገኘናል። ዳዊት “የውስጤ ጭንቀት በበዛ መጠን፣ ማጽናናትህ ነፍሴን ደስ አሰኛት።” (መዝ. 94፥19)። እንዲሁም “እግዚአብሔር ልባቸው ለተሰበረ ቅርብ ነው፤ መንፈሳቸው የተሰበረውንም ያድናቸዋል። የጻድቅ መከራው ብዙ ነው፤ እግዚአብሔር ግን ከሁሉም ያድነዋል።” (መዝ. 34፥18-19) ይላል።

በዚህ የኮሮናቫይረስ ወረርሽኝ ወቅት የእግዚአብሔርን ያህል ልባችንን ሊያጽናና የሚችል ማንም አይገኝም። የእርሱ ማጽናናት አይናወጥም። ማጽናናቱ ማዕበል በበዛበት ባሕር ውስጥ ከማዕበሉ በላይ ከፍ ብሎ እንደሚታይ ዐለት ነው። ይህም ማጽናናት ከቃሉ የሚመጣ ነው፤ – ከመጽሐፍ ቅዱስ።

ምዕራፍ 3

ዐለቱ ጻድቅ ነው

እግዚአብሔር ዐለታችን ከሆነ ጻድቅ ዐለት መሆኑ የማያጠራጥር ነው። ጻድቅ ያልሆነ ዐለት፣ ያለ የሚመስል ግን የሌለ ነገር ነው። ይህ ዓለም ዐቀፍ ወረርሽ በዋነኛነት የሚፈትነው እግዚአብሔር ጻድቅ፣ ቅዱስና መልካም በመሆኑ ላይ ያለንን ርግጠኛነት ነው። ነገር ግን በዚህ ሁሉ መኻል እግዚአብሔር ጻድቅ ዐለት ሊሆነን ካልቻለ፣ ምንም ዐለት የለንም ማለት ነው።

ስለዚህ መጠየቅ የሚገባን ጥያቄ የእግዚአብሔር ጽድቅ፣ ቅድስናና መልካምነት ምንድነው? ብለን ነው። ምክንያቱም እነዚህን የእግዚአብ ሔር ባሕርያት ምንነት በውል ካላወቅን፣ ይህ የኮሮናቫይረስ ወረርሽኝም እንደማይሸረሽራቸው እንዴት ማወቅ ይቻለናል? ወይንም እነዚህ ባሕር ያቱ፣ የሚያድነን ዐለት ዘላለማዊ መሠረቶች መሆናቸውን እንዴት ልናውቅ እንችላለን?

ከዚህ በመቀጠል የምናየው መጽሐፍ ቅዱስ እንዴት የእግዚአብሔርን ቅድስና፣ ጽድቅና መልካምነት በተመሳሰለ መልክ ሳይሆን በተሰና ሰለ (በተቀናጀ) መንገድ እንደ ገለጸልን ነው። ከእግዚአብሔር ቅድስና እንጀመር። እርሱ ምንድነው?

ምጡቅ ፣ ፍጻሜ አልባ ክቡር

በብሉይ ኪዳን መጻሕፍት እንደምናየው ቅድስና ማለት መለየት ነው። ከተራው ነገርና ሁኔታ መለየት። ይህን ትርጉም ወደ እግዚአብሔር ስናመጣው፣ ይህ መለየት በእርሱ ልዩ የመሆን ደረጃ ውስጥ ከእርሱ በቀር ማንም አይገኝም። የእርሱ ልዩ መሆን መለኮታዊ ልዩነት ነው። ለዚህ መለኮታዊ ልዩነት ምጡቅ የሚል ስም ልንሰጠው እንችላ ለን። እርሱ ከሁሉ የተለየ ስለ ሆነ ከሁሉ ይልቅ ምጡቅ ነው። ደግሞም ከሁሉ በላይ የሆነና ከሁሉም በላይ የከበረ ነው።

እግዚአብሔር ሙሴን ዐለቱን እንዲናገረው አዝዞት እርሱ ግን በበትር በመታው ጊዜ፣ እግዚአብሔር ሙሴን ሲገሥጽ፦ “በእስራኤላ ውያን ፊት እኔን ቅዱስ አድርጋችሁ ለማክበር አልታመናችሁብኝም” (ዘኍ. 20፥12) ነበር ያለው። በሌላ አነጋገር ሙሴ እግዚአብሔርን እንደ አንድ በጣም ልዩና እጅግ የታመነ ማንነት ሳይሆን እንደ አንድ ቸል ሊባል እንደሚችል ሰብኣዊ ባለ ሥልጣን ነበር ያየው ማለት ነው።

በሌላ ክፍል ደግሞ፣ በኢሳይያስ 8፥12-13 እግዚአብሔር “እነዚህ ሰዎች፣ ‘አድማ’ ብለው የሚጠሩትን፣ ማንኛውንም ነገር፣ ‘አድማ’ አት በሉ፤ እነርሱ የሚፈሩትን አትፍሩ፤ አትሸበሩለትም። ልትቀድሱ የሚገ

ባው የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔርን ብቻ ነው፤ ልትፈሩት የሚገባው እርሱን ነው፤ ልትንቀጠቀጡለት የሚገባውም እርሱ ነው።" ይላል። በሌላ አባባል እግዚአብሔርን እንዲያው ከምትፈሯቸውና ከምትሸበሩላ ቸው ነገሮች ዝርዝር ውስጥ አውጡት። እርሱ ከሁሉ የላቀ ስለ ሆነ በልዩነትና ከሁሉ በላቀ መንገድ ሊፈራ ሊከበር ይገባዋል።

ስለዚህ የእግዚአብሔር ቅድስና ከሁሉ የሚልቅና ከሁሉ የበለጠ ክብር ያለው ነው። እርሱ ማንም ሊቀርበው በማይደፍረው በራሱ ደረጃ ያለ ነው። እርሱ በሕያውነት ለመኖር የማንም እና የምንም ጥገኛ አይደ ለም። እርሱ በራሱ ፍጹምና ምሉእ ነው። ስለዚህ እርሱ የሁሉም እውነታዎች ምንጭና ባለቤት ነው።

ከሁሉ በላይ ግን ብቸኛ ያልሆነ

እግዚአብሔር ከሁሉም እውነታዎች በላይ ይሁን እንጂ ፍቅር አልባና ፍጹም ብቸኛ ነው ማለት ግን አይደለም። የሥላሴ አስተምህሮ በመጽሐፍ ቅዱስ ከዳር እስከ ዳር ያለ አስተምህሮ ነው። እግዚአብሔር አንድ አምላክ ነው፤ ደግሞም በሦስት መለኮታዊ አካላት ተገልጦ ይኖራል ነው። ግን ሦስት አምላክ አይደለም። ይህ አንድ እግዚአብሔር እጅግ በሚደንቅና ሙሉ በሙሉ ለመረዳት በሚያዳግት የአብ፣ የወልድና የመንፈስ ቅዱስ ኅብረት ውስጥ ይኖራል። ሦስቱም ዘላለማዊ ናቸው፤ መጨረሻም የላቸውም።

ስለዚህ ቅድስናው...እግዚአብሔር የላቀ ክብርና ታላቅነት ባለቤት በመሆኑ ብቸኛና ፍቅር አልባ ሆኖ የሚኖር ነው ማለት አይደለም። እግዚአብሔር አብ፣ ወልድን በሙላት፣ በፍጹምነትና፣ ያለ ልክ ያውቀ

ዋል ደግሞም ይወደዋል (ማር. 1፥11፤ 9፥7፤ ቈላ. 1፥13)። እግዚአብሔር ወልድም እግዚአብሔር አብን በሙላት፣ በፍጹምነትና ያለ ልክ ያውቀዋል ይወደዋልም (ዮሐ. 14፥31)። መንፈስ ቅዱስ ምሉእ፣ ፍጹሙና ልክ አልባው የእግዚአብሔር አብና የእግዚአብሔር ወልድ ፍቅርና ዕውቀት መገለጫ ነው።

ይህን ማወቅ ለምን ይጠቅማል? ምክንያቱም ይህ ፍጹም የሆነ የሥላሴ ኅብረት ለእግዚአብሔር ምሉእነትና ፍጹምነት በጣም አስፈላጊ ነው። ይህ ከሁሉ ለሚልቀው ውበቱ ታላቅነቱና ክብሩ በጣም አስፈላጊ ነው። ይህ ለቅድስናው በጣም አስፈላጊ ነው።

ቅድስና ከጽድቅ ጋር ይሰናሰላል

ከላይ የእግዚአብሔርን ቅድስና ስናይ አንድ ያላነሣነውን ምልከታ እናገኛለን። መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔርን ቅድስና ሲነግረን ከመለየት አንጻር ብቻ ሳይሆን ከግብረገባዊ (ከሞራላዊ) ባሕርይም ጭምር ነው። ለመቀደስ የሚያስፈልገው ልዩ መሆን ብቻ ሳይሆን ትክክል መሆንም ጭምር ነው።

እዚህጋ ኮሮናቫይረስን ከእግዚአብሔር ጋር አያይዘን የምናይበት አንድምታ ላይ ትልቅ ጥያቄ ያስነሣል፦ ጽድቅ ትክክል የሆነውን ነገር ማድረግን የሚያመለክት ከሆነና ትክክል ማድረግ ደግሞ የጽድቅ መስፈርትን ማሟላትን ከጠየቀ፤ በዚህ ወቅት የእግዚአብሔር ጽድቅ የትኛውን መስፈርት ነው የሚያሟላው?

ከፍጥረት በፊት ከእግዚአብሔር በቀር ምንም ዐይነት መስፈርት አልነበረም። እርሱ ያሟላው ዘንድ የሚያሻው አንድም መስፈርት በዙሪ

ያው አልነበረም። ከፍጥረት በፊት እግዚአብሔር ብቻ ብቸኛው እውነታ ነበር። እግዚአብሔር ብቻ በነበረበት ዓለም ለእግዚአብሔር ትክክል ማድረግን እንዴት መወሰን ይቻላል? የእግዚአብሔርስ ቅድስና ልቆ መገኘቱን ብቻ ሳይሆን ጽድቁንም እንዴት ሊያካትት ይችላል?

የዚህ ጥያቄ ቀላል መልስ ለእግዚአብሔር የጽድቁ መስፈርት ራሱ እግዚአብሔር ነው የሚል ነው። ለዚህ መሠረታዊ የመጽሐፍ ቅዱስ መርሕ የሚሆነን፦ “ራሱን መካድ አይችልምና” (2ጢሞ. 2፥13) የሚለው ነው። እርሱ ታላቅነቱን፣ ውበቱንና ክብሩን በሚክድ መንገድ ከቶ አይገኝም። ይህ ለእግዚአብሔር ትክክል የመሆን መስፈርት ነው።

ይህም ማለት የእግዚአብሔር ሞራላዊ የቅድስናው ምልክታ የሆነው ጽድቁ እንደ ታላቅነቱ ውበቱና ክብሩ መጠን የሚመላለስበት የማይለዋወጥ ቀኖርጠኛነቱ ነው። ስለዚህ የእግዚአብሔር የሆነ የትኛውም ፍቅር፣ የትኛውም ሐሳብ፣ የትኛውም ቃልና የትኛውም ድርጊት ሁልጊዜ ከራሱ ገደብ የለሽ ውበትና የላቀ ሙላቱ ጋር በወጥነት ይስማማሉ። እግዚአብሔር የራሱን ክብር፣ ታላቅነትና ውበት ቢክድ ልክ አይሆንም። የመጨረሻው መስፈርትም ይጣሳል። ጻድቅ መሆኑም ይቀራል።

ጽድቅ ከመልካምነት ጋር ይሰናሰላል

የእግዚአብሔር መልካምነት ከቅድስናውና ከጽድቁ ጋር ልዩነት የሌለው አንድ ዐይነት አይደለም። ነገር ግን ቅድስናው በመልካምነቱ ውስጥ ይታያል፤ ጽድቁም መልካምነቱን ይመራል። እርስ በእርስ በፍጹም አይጋጩም።

ሰውን የሚባርክ ነገር ማድረግ የእግዚአብሔር መልካምነት ቸር የመሆኑ ማንነት ውስጥ ያለው ባሕሪው ነው ። የእግዚአብሔር የላቀ ሙላቱና ፍጹምነቱ እርሱም ቅድስናው እንደሚፈስ ምንጭ ነው። ስለዚህም ቸር ነው። እግዚአብሔር የምንም ነገር እጥረት የለበትም። መቼም ቢሆን እርሱ የጐደለውን ሌሎችን በመጠቀም ሞልቶ አያውቅም። ይልቁንም፣ የእርሱ ባሕሪ መስጠት ነው፤ ከቶ መውሰድ አይደለም። “እርሱ ለሰዎች ሁሉ ሕይወትንና እስትንፋስን እንዲሁም ሌላውንም ነገር ሁሉ የሚሰጥ ስለሆነ፣ የሚጐድለው ነገር ባለመኖሩ በሰው እጅ አይገለገልም።” (ሐ.ሥ. 17፥25)።

ነገር ግን ይህ የእርሱ መልካምነት ከርሱ ጽድቅ የተለያየ አይደለም። ትልቅነቱን፣ ክብሩንና፣ ወደር አልባነቱንም በሚጥስ መልኩ የተሰጠ አይደለም። ስለዚህም ምክንያት የእግዚአብሔር ጽድቅ ቅጣትም መልካ ምነትም አለበት። እግዚአብሔር ንስሓ የማይገቡትን በሲያል በሚቀጣበት ጊዜ መልካምነቱን ለእነርሱ አይሰጥም። መልካም መሆኑን ግን አያቆምም። ቅድስናውና ጽድቁ የመልካምነቱን ስጦታ ገደብ ይወስናሉ።

ለዚህም ነው መልካምነቱ በተለይ ወደሚፈሩትና እርሱን መጠጊያ ወዳደረጉት የምትፈሰው። “በሰዎች ልጆች ፊት፣ ለሚፈሩህ ያስቀመጥ ሃት፣ መጠጊያ ላደረጉህም ያዘጋጀሃት፣ በጎነትህ ምንኛ በዛች!” (መዝ. 31፥19)።

ይህ አክብሮትና እምነት የእግዚአብሔርን መልካምነት እንደ ክፍያ አያስገኙም። ውሱንና፣ ሙሉ በሙሉ ጥገኛ የሆኑት ኀጢአተኛ የሆኑ የሰው ልጆች ምንም ዐይነት ነገር ከእግዚአብሔር እንደ መብት ሊያገኙ አይችሉም። ለኀጢአተኞች የእግዚአብሔር መልካምነት ሁልጊዜ ነጻ

እና የማይገባቸው ነው። ታዲያ እግዚአብሔር እርሱን ለሚፈሩትና እርሱን መጠጊያ ለሚያደርጉት ሰዎች ብዙ መልካምነቱን የሚያሳየው ለምንድነው? ምክንያቱም እንዲህ ያለ አክብሮት እና እምነት የእግዚአብሔርን ክብር፣ ውበትና ታላቅነት ስለሚያሳዩ (ሮሜ 4፥20)። ስለዚህ የእግዚአብሔር ጽድቅ እንደዚህ ዐይነቱን እግዚአብሔርን የሚያከብር አመለካከት ትክክለኛነቱን እንዲያረጋግጥ ያነሣሣዋል።

ይህ ስለ ኮሮናቫይረስ ምንድነው?

በቀጣዩ ምዕራፍ ስለ እግዚአብሔር ሁሉን ዐዋቂነት፣ ሁሉን ገዥነቱና ከሁሉም በላይ ሉአላዊ ስለ መሆኑ እናያለን። በዚህ ክፍል ያየነው ነገር በኮሮናቫይረስ ወቅት የሚገለጠውን የእግዚአብሔር ጣት፣ የመልካምነቱን፣ የጻድቅነቱንና የቅድስናውን ማንነት ዝቅ የሚያደርግ መደምደሚያ ከመሥራት ይጠብቀናል። የሰውን ሥቃይ ከመለኮታዊ ክፋት ጋር ለማያያዝ ያን ያክል ደፋር አንሆንም። ወይም ደግሞ እግዚአብሔር ዓለምን ሲያስተዳድር ቅዱስና መልካም መሆኑን ያቆማል ወደሚል መደምደሚያም አንሄድም።

ሁላችንም ኀጢአተኞች ነን። ልዩነትም የለም። ሁላችንም የእግዚአብሔርን ክብር፣ ውበትና ታላቅነት በምንደሰትባቸው ሌሎች ነገሮች ለውጠናል (ሮሜ 1፥23፤ 3፥23)። ቢጸጽተንም ባይጸጽተንም ይህ እጅግ አሳፋሪና የእግዚአብሔርን ክብር የሚያቃልል ድርጊት ነው። ስለ ዚህ ሁላችንም ቅጣት ይገባናል። ይህ የእግዚአብሔርን ክብር ማቃለላ ችን ከቀኣጣ በታች እንድንሆን አድርጎናል። መጽሐፍ ቅዱስ እኛ "የቀኣጣ

ልጆች ነበርን” (ኤፌ. 2፥3) ይለናል። ይህም ማለት እግዚአብሔር ከእኛ ላይ መልካምነቱን ቢያነሣ እንኳ እርሱ ግን ቅዱስና ጻድቅ እንደ ሆነ ይኖራል ማለት ነው።

ስለዚህ ኮሮናቫይረስ ቅድስና፣ ጽድቅና፣ መልካምነት የጐደለው እግዚአብሔር መኖሩን አያመለክትም። ዐለታችን በነዚህ አስጨናቂ ቀናቶችም ውስጥ ቢሆን እንኳ ጻድቅና ቅዱስ የማይሆን አይደለም። “እንደ እግዚአብሔር ያለ ቅዱስ ማንም የለም፤... እንደ አምላካችን ያለ ዐለት የለም።” (1ሳሙ. 2፥2)። ዐለታችን ያለ የሚመስል ነገር ግን የሌለ አይደለም።

ምዕራፍ 4

ከሁሉ በላይ ሉዓላዊ

በምዕራፍ ሁለት ውስጥ “መራራ መግቦት” የሚል ሐረግ ተጠቅሜ ነበር። ይህም የኮሮናቫይረስ ምንነትን የሚገልጽ ሃረግ ነው። የተወሰኑ የእግዚአብሔርን ሥራዎች መራራ ብሎ መግለጽ እግዚአብሔርን መሳ ደብ አይደለም። የሩት ዐማት የሆነችው ኑኃሚን፣ ባለቤቷን፣ ሁለት ልጆቿዋንና አንድ ምራቷን በረኃብና በስደት ካጣች በኋላ ያለችው፡-

“ሁሉን የሚችል አምላክ ሕይወቴን እጅግ መራራ አድርጎታልና... በሙላት ወጣሁ፤ ነገር ግን እግዚአብሔር ባዶዬን መለሰኝ እግዚአብ ሔር አስጨንቆኝ፣ ሁሉን የሚችል አምላክ መከራ አምጥቶብኝ ሳለ” (ሩት 1፥20-21)

እየዋሸች፣ እያጋነነች ወይንም እግዚአብሔርን እየወነጀለች አልነበ ረም። የሚያስጨንቅ ቢሆንም እውነታ ነበር። “መራራ መግቦት” ማለት የእግዚአብሔርን መንገድ ማንኳሰስ አይደለም ይልቁንም፤ አገላለጽ ነው።

ደግሞም በእንደዚህ ዐይነት መራራ መግቦት ውስጥ የእግዚአ ብሔር ቃል ጣፋጭነቱን እንደማያጣ በምዕራፍ ሁለት ላይ ተናግሬ ነበር - “ሐዘንተኞች ስንሆን ሁልጊዜ ደስተኞች ነን።” (2ቆሮ. 6፥10) የሚለ ውን ቃል ምስጢር ከተረዳን። ወደዚህ ምስጢር በድጋሚ እንደምን መለስ ተናግሬ በአንድ ዐረፍተ ነገር እንዲህ ብዬ ጠቅልዬው ነበር፡- *“ኮሮናቫይረስን ማቆም የሚችል ግን ያላቆመ ያው ሉዓላዊነት በዚያው ወቅት ውስጥ ሕይወትን የሚያስቀጥልና የሚደግፍ ነው።”* ይህን ማወቅ ሁሉንም ልዩነት ይፈጥራል። ይህ እውነት ነውን?

እግዚአብሔር የፈቀደውን ያደርጋል

እግዚአብሔር ሁሉን ገዢና በሁሉ ጥበበኛ መሆኑን ማሳየት የዚህና የሚቀጥለው ምዕራፍ ዐላማ ነው። እርሱ በኮሮናቫይረስ ላይ ሉዓላዊ ነው። በርግጥም ይህን መልካም ዜና እነግራችሁ ዘንድ እወ ዳለሁ—ይህም በመራራ መግቦቱ ውስጥም ቢሆን የእግዚአብሔርን ጣፋጭነት የመለማመድን ምስጢር ነው።

እግዚአብሔር ሁሉን ይገዛል ማለት እርሱ ሉዓላዊ ነው ማለት ነው። የእርሱ ሉዓላዊነት ማለት በፈቃዱ ውሳኔ፣ እንዲሆን የወሰነውን ሁሉ ማድረግ ይችላል፤ ደግሞም ያደርጋል ማለት ነው። *በውሳኔ* ያልሆኑት እግዚአብሔር ራሱ ባይፈጽማቸውም፣ እንዲሆኑ የሚፈቅዳቸው ነገሮች አሉ ማለቴ ነው። ሊፈጽም የማይፈልገውን መግለጽ ይችላል። ስለዚህ እነዚህ ውሳኔዎች አይደሉም። እርሱ ራሱ እንዲህ ዐይነቱን ፈቃድና ምኞት ወደ መፈጸም ደረጃ እንዲደርሱ አያደርጋቸውም።

ለምሳሌ ሰቆቃው ኤርምያስ 3፥32-33ን እናስብ፦

“መከራን ቢያመጣ እንኳ ይራራል፤
ታላቅ ፍቅሩ ኢይለወጥምና ሆን ብሎ ችግርን፣
ወይም መከራን በሰው ልጆች ላይ ኢያመጣ ምና።”
እርሱ መከራን ያመጣብናል ግን ከልቡ ኢይደለም።

ይህም ማለት ወደ እኛ መከራን ከማምጣት በተቃራኒ የሚያጋድል ባሕሪ (ልብ) ቢኖ ረውም፤ ሌሎች የባሕርዩ ገጽታዎች እነርሱም ጽድቁና ቅድስናው መከራ እንዲመጣብን ያስገድዱታል።

እርሱ በሁለት ሐሳብ መካከል የሚያመነታ ኢይደለም። በእርሱ ባሕርያት ቅንጅት ውስጥ ፍጹም ውበትና ቅንብር አለ። ግን ውስብስ ብነት የለውም ማለትም አይደለም። የእርሱ ባሕርይ አንድ ሰው ከሚጫ ወተው የሙዚቃ መሳሪያ ይልቅ የተለያዩ እና ብዛት ያላቸው የሙዚቃ መሳሪያዎች ስብስብ የያዘ አንድ ቡድን (ኦርኬስትራን) ይመስላል።

እርሱ ሉዓላዊ ነው ማለት በፈቃዱ ውሳኔ እንዲሆን የወሰነውን ሁሉ ማድረግ ይችላል፤ ደግሞም ያደርጋል ማለት ነው ስል፣ ከእርሱ ውጪ የሆነ ፈቃዱን ከመሆን የሚያሰናክል ወይም የሚከለክል አንዳች ኀይል የለም ማለቴ ነው። ነገሮች እንዲሆኑ ሲወስን ነገሩ ይሆናል። በሌላ አነጋገር የሆነው ነገር ሁሉ የሆነው እርሱ እንዲሆን ስለ ፈቀደ ነው።

በነገሮች ሁሉ ሉዓላዊ

ኢሳይያስ ይህ ባሕርዩ (ሉዓላዊነቱ) እግዚአብሔርን አምላክ የሚያ ሰኘው መሠረታዊ ባሕርዩ እንደ ሆነ ያስተምራል፦

“የጥንቱን፣ የቀደመውን ነገር አስታውሱ፤ እኔ አምላክ ነኝ፤ ከእኔም በቀር ሌላ የለም፤ እኔ አምላክ ነኝ፤ እንደ እኔ ያለ የለም። የመጨረሻውን ከመጀመሪያው፣ ገና የሚመጣውንም ከጥንቱ ተናግሬ አለሁ፤” (ኢሳ. 46፥9-10)

አምላክ መሆን ማለት የራሱን ምክር ጸንቶ እንዲቆም ማድረግ ነው— ሁልጊዜም። እግዚአብሔር የወደ ፊት ክሥተቶችን እንደሚከሠቱ ብቻ አይናገርም፤ ይልቁንም እውን ያደርጋቸዋል። እርሱ ቃሉን ይናገራል፤ ደግሞም “ቃሌን እፈጽመው ዘንድ እተጋለሁ” (ኤርምያስ 1፥12) ይላል።

ይህም ማለት ኢዮብ በከባድ መንገድ እንደ ተማረው “አንተ ሁሉን ማድረግ እንደምትችል፣ ዕቅድህም ከቶ እንደማይሰናከል ዐወቅሁ።” (ኢዮ. 42፥2) ወይም ናቡከደነፆር ምሕረት ካገኘው ውርደቱ በኋላ እንደ ተማረው፡-

“የምድር ሕዝቦች ሁሉ፣ እንደ ኢምንት ይቈጠራሉ፤ በሰማይ ኀይላት፣ በምድርም ሕዝቦች ላይ፣ የወደደውን ያደርጋል፤ እጁን መከልከል የሚችል የለም፤ ‘ምን ታደርጋለህ?’ ብሎ የሚጠይቀውም የለም።” (ዳን. 4፥35)

ወይም መዝሙረኛው እንዳለው፡-

“በሰማይና በምድር፣ በባሕርና በጥልቅ ሁሉ ውስጥ፣እግዚአብሔር ደስ ያሰኘውን ሁሉ ያደርጋል።” (መዝ. 135፥6)

ወይም ደግሞ ሐዋርያው ጳውሎስ እንደ ጠቀለለው፡-

“ሁሉን በፈቃዱ ምክር መሠረት እንደሚሠራው”
(ኤፌ. 1፥11)

“ሀሉን” እንጂ የተወሰኑ ነገሮችን አይደለም። “በፈቃዱ” እንጂ እንደ ውጫዊ ጎይል ወይም ፈቃድ አይደለም።

በሌላ አገላለጽ ይህ የእግዚአብሔር ሉዓላዊነት ሁሉን የሚያካትትና በሁሉ ሁኔታ ላይ የሚሠለጥን ነው ማለት ነው። እርሱ የዚህን ዓለም የበላይነት ይዟል። ነፋሳትን (ሉቃ. 8፥25)፣ ብርሃናትን (ኢዮ. 36፥32)፣ ውርጭን (መዝ. 147፥16)፣ ጓጉንቸሮችን (ዘፀ. 8፥1-15)፣ አንበጣዎችን (ዘፀ. 10፥1-20)፣ ትሎችን (ዮና. 4፥7)፣ ዓሣን (ዮና. 2፥10)፣ ድንቢጦችን (ማቴ. 10፥29)፣ ሣርን (መዝ. 147፥8)፣ ተክሎችን (ዮና. 4፥6)፣ ራብን (መዝ. 105፥16)፣ ፀሓይን (ኢያ. 10፥12-13)፣ የእስር ቤት በሮችን (ሐ.ሥ. 5፥19)፣ ዕውርነትን (ዘፀ. 4፥11፤ ሉቃ. 18፥42)፣ ደንቁሮነትን (ዘፀ. 4፥11፤ ማር. 7፥37)፣ ሽባነትን (ሉቃ. 5፥24-25)፣ ንዳድን (ማቴ. 8፥15)፣ ሁሉን ሕመሞችን (ማቴ. 4፥23)፣ የኑዛ ዕቅዶችን (ያዕ. 4፥13-15)፣ የነገሥታትን ልብ (ምሳ. 21፥1፤ ዳን. 2፥21)፣ ሕዝብን (መዝ. 33፥10)፣ ነፍሰ ገዳዮችን (ሐ.ሥ. 4፥27-28)፣ መንፈሳዊ ሙታንን (ኤፌ. 2፥4-5) ይገዛል፤ ሁሉም ሉዓላዊ ፈቃዱን ይፈጽማሉ።

እግዚአብሔርን በስሜታዊነት የምንመለከትበት ወቅት አይደለም

ስለዚህም ኮሮናቫይረስ በእግዚአብሔር የተላከ ነው። ይህ ወቅት ስለ እግዚአብሔር በስሜታዊነት የምንመለከትበት ወቅት አይደለም።

ከዚህ ይልቅ መራራ ወቅት ነው። እግዚአብሔር አዝዞታል። እግዚአብሔር እየገዛው ነው። ደግሞም እርሱ ማብቂያን ያበጅለታል። የኮሮና ቫይረስ እንቅስቃሴዎች ሁሉ ከእግዚአብሔር ቍጥጥር ውጪ አይደሉም። ሕይወትና ሞት በእርሱ እጅ ነው። ኢዮብ የሚከተለውን በተናገረ ጊዜ በከንፈሩ አልበደለም፦

“ዕራቍቴን ከእናቴ ማሕፀን ወጣሁ፤ ዕራቍቴንም እሄዳለሁ። እግዚአብሔር ሰጠ፤ እግዚአብሔር ነሣ፤ የእግዚአብሔር ስም ቡሩክ ይሁን።” (ኢዮ. 1፥21)

እግዚአብሔር ሰጠ። እግዚአብሔር ነሣ። እግዚአብሔር የኢዮብን ዐሥር ልጆች ነሣ።

የምንተነፍሰው እያንዳንዱ ትንፋሽ የጸጋው ስጦታ እንጂ በእግዚአብሔር ፊት አንድም በሕይወት የመኖር መብት ያለው ሰው የለም። እያንዳንዱ የልብ ምት የእርሱን ደጋፍ ይሻል፤ ሞትና ሕይወት በእርሱ እጅ ነውና፦

“እኔ ራሴ እርሱ እንደ ሆንሁ እዩ፤ ከእኔም በቀር ሌላ አምላክ የለም፤ እገድላለሁ፤ አድናለሁም፤ አቈስላለሁ፤ እፈውሳለሁም፤ ከእጄም የሚያስጥል ማንም የለም።” (ዘዳ. 32፥39)

ስለዚህ ስለ ኮሮናቫይረስም ይሁን ስለ ሌላ ሕይወትን አደጋ ላይ ስለሚጥል ነገር ስናስብ እንዴት ማሰብ እና መናገር እንዳለብን ያዕቆብ ይነግረናል፦

“የጌታ ፈቃድ ቢሆን እንኖራለን፤ ይህን ወይም ያንን እናደርጋለን” ማለት ይገባችኋል። (ያዕ. 4፥15)

ቢፈቅድ እንኖራለን፤ ባይፈቅድ አንኖርም።

እስከማውቀው ድረስ፣ ይህ መጽሐፍ ሲታተም በሕይወት አልኖር ይሆናል። ቢያንስ አንድ ዘመዴ በኮሮናቫይረስ ተይዟል። እኔም ሰባ አራት ዓመቴ ነው። ሳንባዎቼም በደም መርጋትና በብሮንካይተስ (ከወቅቶች ለውጥ ጋር በሚቀሰቀስ የአየር ቧንቧ ህመም) በቀላሉ በበሽታ ለመያዝ የተጋለጡ ናቸው። ሆኖም ግን እነዚህ እውነታዎች፣ መኖሬን አይወስኑም፤ እግዚአብሔር ግን ይወስናል። ይህ መልካም ዜና ነው? አዎን! ለምን መልካም ዜና እንደ ሆነ በሚቀጥለው ምዕራፍ ለማሳየት እሞክራለሁ።

ምዕራፍ 5

የአገዛዙ ምቹነት

የእግዚአብሔርን ከኮሮናቫይረስም ይሁን ከኔ ሕይወት በላይ ሉዓላዊ የመሆኑን ዜና ለምን ውብ ትምህርት አድርጌ መቀበል ይኖርብኛል? ምስጢሩ "*ኮሮናቫይረስን ማቆም የሚችል ማን ያላቆመ፣ ያው ሉዓላዊነት በዚያው ወቅት ውስጥ ሕይወትን የሚቀጥልና የሚደግፍ መሆኑን ማወቅ ነው*" ብዬ ነበር። በሌላ አገላለጽ፣ የእግዚአብሔርን ሉዓላዊነት ከመከራ ላይ የምናነሣ ከሆነ፣ ሁሉንም ነገር ወደ መልካም መለወጥ የሚችል ሉዓላዊ መሆኑን እናጣለን።

እግዚአብሔርን ከሉዓላዊነቱ ማንሣት መልካም ዜና አይደለም

በበሽታ ላይ የሚሠለጥን ያው ሉዓላዊነት በማጣት ውስጥም የሚ ደግፍ ነው። ሕይወትን የሚነጥቅ ያው ሉዓላዊነት በሞት ላይ የሚነግ ሥና አማኞችን ወደ ክርስቶስና ወደ ዘላለማዊ ቤት የሚያመጣም ነው።

ሰይጣን፣ ሕመም፣ ተንኮል፣ ዕድል ወይም ዕጣ ፈንታ በኔ ሕይወት ላይ የመጨረሻ ወሳኝ ናቸው ብሎ ማሰብ ደስ አይልም። ይህ መልካም ዜና አይደለም።

የእግዚአብሔር አገዛዝ ግን መልካም ዜና ነው። ለምን? ምክንያቱም እግዚአብሔር ቅዱስ፣ ጻድቅና መልካም ስለ ሆነ። ደግሞ እርሱ ያለ ልክ ጠቢብ ነው። "ጥበብና ኀይል የእግዚአብሔር ናቸው፤ ምክርና ማስተዋልም በእርሱ ዘንድ ይገኛሉ።" (ኢዮ. 12፥13)። "ለጥበቡም ወሰን የለውም።" (መዝ. 147፥5)። "የእግዚአብሔር የጥበቡና የዕውቀቱ ባለጠግነት እንዴት ጥልቅ ነው!" (ሮሜ 11፥33)። የእርሱ ትልቅ ዕላማ "ዕሳቡም በአሁኑ ዘመን በቤተ ክርስቲያን አማካይነት ብዙ ገጽታ ያለው የእግዚአብሔር ጥበብ በሰማያዊ ስፍራ ላሉት አለቆችና ባለ ሥልጣናት ይታወቅ ዘንድ ነው፤" (ኤፌ. 3፥10) የሚለው ነው።

ምንም ነገር አያስደንቀውም፣ አያደናግረውም ወይም ግራ አያጋባ ውም። መጠን የሌለው ኀይሉ የሚያርፈው መጠን በሌለው ቅድስናው፣ ጽድቁና መልካምነቱ ላይ ነው - በጥበቡ ላይ ነው። እነዚህ ሁሉ በልጁ በክርስቶስ ያመኑትን ለማገልገል የቆሙ ናቸው። እግዚአብሔር ለጎጢአ ተኞች እንዲሞት በላከው በኢየሱስ የሠራው ሥራ ስለ ኮሮናቫይረስም ሁሉ ነገር አለው።

እንዴት እግዚአብሔር "ሁሉን ነገር" ለጎጢአተኞች ጠብቆ እንዳቆየ

ነገሩ እንዲህ ነው። በሮሜ 8፥32 ላይ "ለገዛ ልጁ ያልሳሳለት፣ ነገር ግን ለሁላችንም አሳልፎ የሰጠው እርሱ፣ ሁሉንስ ነገር ከእርሱ ጋር እንደ

ምን በልግስና አይሰጠን?” ይላል። ይህም ማለት እግዚአብሔር በእኛ ፈንታ እንዲሠዋ ልጁን ለመላክ መፍቀዱ ሙሉ ሉዓላዊነቱን በመጠቀም “ሁሉን ነገር” ለእኛ እንደሚሰጠን ማረጋገጫና ዐዋጅ ነው። “ሁሉንስ ነገር ከእርሱ ጋር እንደ ምን በልግስና አይሰጠን?” ማለትም እርሱ በርግጥም ይሰጠናል። በልጁ ደም ዋስትና የተረጋገጠ ነው።

እነዚህ “ሁሉ ነገር” የተባሉት ነገሮች ምንድን ናቸው? ፈቃዱን ለማድረግ፣ ስሙን ከፍ ከፍ ለማድረግ እና በደኅና ወደ እርሱ መገኘት ለመድረስ የሚያስፈልጉን ነገሮች ናቸው።

ከሦስት ቀኖሮች በኋላ ጳውሎስ ይህ እንዴት በእውነተኛ ዓለም ውስጥ እንደሚሠራ አብራርቶታል - በኮሮናቫይረስም ውስጥ። የእግዚአብሔር ማለቂያ የሌለውና በደም የተመሠረተው “ሁሉን ነገር” ለእኛ የመስጠት ቀናዒነት ኮሮናቫይረስን ሲገናኘው ምን ይመስላል? ጳውሎስ እንዲህ ይላል፦

> “ከክርስቶስ ፍቅር የሚለየን ማን ነው? ችግር ነው ወይስ ሥቃይ፣ ወይስ ስደት፣ ወይስ ረኃብ፣ ወይስ ዕራቍትነት፣ ወይስ አደጋ ወይስ ሰይፍ [ወይስ ኮሮናቫይረስ]? ይህም፣ “ስለ አንተ ቀኑን ሙሉ ከሞት ጋር እንጋፈጣለን፤ እንደሚታረዱ በጎች ተቈጠርን” ተብሎ እንደ ተጻፈ ነው። ምንም አይለየንም፤ በዚህ ሁሉ በወደደን በእርሱ ከአሸናፊዎች እንበልጣለን።” (ሮሜ 8፥35-37)

“ስለ አንተ ቀኑን ሙሉ ከሞት ጋር እንጋፈጣለን” የሚለውን የሚያምፅ፣ ግን አስደናቂ ቃል እንዳታልፉት። ይህም ማለት ለገዛ ልጁ

እንኳን ስላልሳሳለት፤ የሚሰጠን “ሁሉን ነገር” በደኅና በሞት በኩል ወደ እርሱ መሰብሰብን ጭምር ያካትታል። ወይም በሮሜ 8፡38-39 እንዳለው “ይህን ተረድቻለሁ፤ ሞትም ይሁን ሕይወት፣ . . . በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ካለው ከእግዚአብሔር ፍቅር ሊለየን አይችልም።”

ሰይጣንና ክፋት

ምንም እንኳ ሰይጣን በመለኮታዊ ልጓም ቁጥጥር ስር ሆኖ በመከራችንና በሞታችን ውስጥ እጅ ቢኖረውም፤ እርሱ የመጨረሻ ውሳኔ ሰጪ አይደለም። ያለ እግዚአብሔር ፈቃድና ገደብ ሊጐዳን አይችልም (ኢዮ. 1፥12፤ ሉቃ. 22፥31፤ 2ቆሮ. 12፥7)። በመጨረሻ ግን፣ ዮሴፍ ለባርነት ለሸጡት ወንድሞቹ ያላቸውን እኛም ለሰይጣን የማለት መብት አለን፡- “እናንተ እኔን ለመጒዳት ዐስባችሁ አድርጋችሁት ነበር፤ እግዚአብሔር ግን ዛሬ እንደሚታየው ሁሉ የብዙዎችን ሕይወት ለማዳን ለበጎ ነገር አዋለው።”

ይህን ዝቅ አድርገን እንዳንረዳው ልንጠነቀቅ ይገባል። ቃሉ “እግዚአብሔር ወደ በጎ ለወጠው” ወይም “እግዚአብሔር በጎ አደረገው” አይልም። “እግዚአብሔር ለበጎ ነገር አዋለው” ነው የሚለው። እነርሱ ክፉ ዕቅድ ነበራቸው፤ እግዚአብሔር ግን በጎ ዕቅድ ነበረው። እግዚአብሔር ገና ከነገሩ ጅማሮ ዐላማና ትርጒም ነበረው እንጂ ድንገት በዚህ የኃጢአት ጒዳይ መኻል ገብቶ ነገሮችን ማስተካከል አልጀመረም። ከመጀመሪያው ጀምሮ ለበጎ እያዋለው ነበር።

የሰውና የሰይጣን ክፋት መከራችንን ሲያከብዱት፤ ለመጽናናት ይህ በጣም ቍልፍ ነው። በክርስቶስ ሆነን ለሰይጣን (ለክፉ ሰዎች) እንዲህ የማለት መብት አለን፦ “እናንተ ለክፋት አደረጋችሁት። እግዚአ ብሔር ግን ለበጎ ነገር አዋለው።” ሰይጣን፣ ሕመም ወይም ክፉ ሰዎች ሉዓላዊ አይደሉም። ሉዓላዊ እግዚአብሔር ብቻ ነው። እርሱ መልካም እና ጠቢብ - ሉዓላዊም ነው።

ድንቢጥን ሳይሆን እያንዳንዱን ጠጕር

ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ የእግዚአብሔርን አስደናቂ ሉዓላዊነት ውብ አድርጎ ሲገልጥላቸው እንዲህ ይላል፦

> “በአንድ ሳንቲም ከሚሸጡት ሁለት ድንቢጦች አንዲቷ እንኳ ያለ አባታችሁ ፈቃድ ምድር ላይ አትወድቅም። የራስ ጠጕራ ችሁ እንኳ አንድ ሳይቀር የተቈጠረ ነው። ስለዚህ አትፍሩ፤ ከብዙ ድንቢጦች ይልቅ ዋጋችሁ የከበረ ነው።” (ማቴ. 10፥ 29-31)

በእግዚአብሔር ፈቃድ ካልሆነ በቀር አንዲትም ድንቢጥ በምድር ላይ አትወድቅም። የትኛውም ቫይረስ በእግዚአብሔር ፈቃድ ካልሆነ በቀር አይንቀሳቀስም። ይህ እጅግ ረቂቅ ሉዓላዊነት ነው። ከዚያ በመቀጠል ኢየሱስ ምን ነበር ያለው? ሦስት ነገሮችን፦ ከብዙ ድንቢጦች ይልቅ ዋጋችሁ የከበረ ነው። የራስ ጠጕራችሁ እንኳ አንድ ሳይቀር የተቈጠረ ነው። አትፍሩ።

ለምን አንፈራም? ምክንያቱ የእግዚአብሔር ረቂቅ ሉዓላዊነት—ብንኖርም ብንሞትም–የእርሱን ቅድስና፣ ጽድቅ፣ መልምነትና ጥበብ ስለሚያሳየን ነው። በክርስቶስ ዋጋ እንደሌላቸው ነገሮች አልሆንም፤ ይልቅስ ዋጋችን የከበረ ልጆቹ ነን። “ከብዙ ድንቢጦች ይልቅ ዋጋችሁ የከበረ ነው።” ይላልና።

ቀደም ብዬ የጠቀስሁት ምስጢር ይህ ነው፡- *ኮሮናቫይረስን ማቆም እየቻለ ያላቆመው ያው ሉዓላዊነት በዚያው ወቅት ውሰጥ ሕይወትን የሚያስቀጥልና የሚደግፍ መሆኑን መረዳት።* ይህ ብቻም አይደለም ሁሉም ነገር፣ መራራ ሆነ ጣፋጭ፣ አንድ ላይ ተያይዘው ለበጎ የሆነን ነገር እንዲሠሩልን እናውቃለን—እግዚአብሔርን ለሚወዱ በክርስቶስ ለተጠሩ የሚጠቅምና ለበጎ ይደረጋሉ። (ሮሜ 8፥28-30)።

ሥራዬን እስከምጨርስ ድረስ አልሞትም

በሞት ፊት እንደ ዐለት የጠነከረ እንደዚህ ዐይነት ርግጠኛነት በክርስቶስ የሆኑትን ለሁለት ሺሕ ዓመታት ሲያበረታታቸው ኖሯል። የእግዚአብሔር ጠቢብና መልካም ሉዓላዊነት እውነታ በሺሕዎች ለሚ ቁጠሩ ክርስቲያኖች በፍቅር መሥዋዕትነት ውስጥ የማይዋዥቅ ኀይላ ቸው ሆኗል።

ለምሳሌ ሄንሪ ማርቲን የተባለ ወደ ሕንድ እና ፐርሺያ አገር የተላከ ሚሲዮናዊ፤ በሠላሳ አንድ ዓመቱ (እ.አ.አ ኦክቶበር 16 ቀን 1812) ከኮሮናቫይረስ ጋር በሚመሳሰል ወረርሽኝ በሽታ ሕይወቱ ያለፈ ሰው በወርኀ ጥር 1812 በግል ማስታወሻው ላይ ይህን ጽፎአል፡-

> “በሁሉ ነገር ይህ ዓመት እስከ ዛሬ ካየኋቸው ሁሉ በአደጋ የተሞላ ይሆንብኛል፤ ነገር ግን የፐርሺያኛን ዐዲስ ኪዳን ለመ ጨረስ የምኖር ከሆነ ከዚያ በኋላ ያለው ሕይወቴ ያን ያክል አስፈላጊ አይሆንም። ግን ሕይወት ወይም ሞት የእኔ ቢሆን፣ ክርስቶስ በእኔ ይከበር! እርሱ ለእኔ እሠራው ዘንድ ሥራ ካለው ግን ልሞት አልችልም።”[2]

ይህም ብዙ ጊዜ “በእኔ ያለው የክርስቶስ ሥራ እስኪያልቅ ድረስ አልሞትም” በሚለው ተተክቶ ጥቅም ላይ ይውላል። ይህ ጥልቅ እውነት ነው። እንዲሁም ሕይወትና ሞት በሉዓላዊው አምላካችን እጅ ላይ በመሆናቸው እውነታ ላይ ሳይዛነፍ የሚያርፍ ነው። ሰባት ዓመት ቀደም ብሎ ማርቲን በሃያ አራት ዓመቱ የሚከተለውን ጽፎ ነበር፦

> እግዚአብሔር የአጽናፈ ዓለሙ ሉዓላዊ ባይሆን ኖሮ፣ ምን ያክል ጐስቋላ እሆን ነበር! ነገር ግን ጌታ ገዢ ነውና ምድር ደስ ይበላት። የክርስቶስም መንገድ ያሸንፋል። ነፍሴ ሆይ በተስፋው ደስ ይበልሽ።[3]

ክፍል 2

እግዚአብሔር በኮሮናቫይረስ ምን እየሠራ ነው?

ቀዳሚ ሐሳብ፦
ማየትና ማመልከት

በርግጥም እግዚአብሔር ከሉዓላዊ ሥልጣኑ ስላልተነሣ “ሁሉን በፈቃዱ ምክር መሠረት” (ኤፌ. 1፥11) ይገዛል። ይህም ኮሮናቫይረስ ከዚህ ሁሉ ጥፋቱ ጋር በእግዚአብሔር ቅዱስ፣ ጻድቅ፣ መልካም እና ጠቢብ እጆች ከተያዘ፣ ታዲያ እግዚአብሔር በዚህ ውስጥ ምን እየሠራ ነው? ዐላማውስ ምንድነው?

በሰው አትታመኑ

ይህን ጥያቄ ከመመለስ በፊት መባል ያለበት ጉዳይ፣ ከእግዚአብሔር ጥበብ ጋር ሲነጻጸር የእኔ አመለካከት ከምንም የማይቈጠር መሆኑ ነው። የእናንተም እንደዚያው። ከራሳችን አእምሮ የምናስበው ነገር ፋይዳው እምብዛም ነው። መጽሐፍ ቅዱስ “በራሱ የሚታመን ተላላ ነው” (ምሳ. 28፥26) ይላል። ይልቁንም “በፍጹም ልብህ በእግዚአብሔር ታመን፤ በራስህ ማስተዋል አትደገፍ” (ምሳ. 3፥5) ።

እኛ ሰዎች ውሱኖች፣ ኀጢአተኞች፣ እንደየባህሉ የተቃኘንና የዘረ መላችን (Genes) እና የግል ታሪኮቻችን ተጽዕኖ ያለብን ነን። ከልባችን፣ ከአእምሮአችንና ከአፋችን የራሳችንን ምርጫዎች ምክንያታዊ የምናደ ርግበት መንገዶች ይወጣሉ። ስለዚህ ነቢዩ ኢሳይያስ ለተናገረው ትንቢት ብንሰጥ ጠቢባን እንሆናለን፦ “እስትንፋስ አፍንጫው ላይ ባለች በሰው አትታመኑ፤ ከቶ ምን የሚበጅ ነገር አለው!” (ኢሳ. 2፥22)።

ታዲያ ይህን መጽሐፍ መጻፌ ብሎም “እግዚአብሔር በኮሮናቫይረስ ምን እየሠራ ነው” የሚል ክፍል ማካተቴ ግምት አይሆንብኝምን?

በፍጹም አይሆንም። እግዚአብሔር በመጽሐፍ ቅዱስ ባይናገር ኖሮ፤ እኛ በእውነት (በከፊልም ቢሆን) እርሱን እና መንገዶቹን እንድናውቅ እግዚአብሔር በሰዎች ቃላት ባይናገር ኖሮ፣ የጳውሎስ፦ “ጸጋውንም በጥበብና በማስተዋል ሁሉ አበዛልን፤ በክርስቶስ ያቀደውንም የፈቃዱን ምስጢር እንደ በጎ ሐሳቡ እንድናውቅ አደረገ።” የሚለው ቃል እውነት ባይሆን ኖሮ፣ ደግሞም፥ “እንግዲህ ይህን ስታነቡ፣ የክርስቶስን ምስጢር እንዴት እንደማስተውል መረዳት ትችላላችሁ።” (ኤፌ. 3፥4) በማለት ባይናገር ኖሮ፣ በእርግጥ ግምት ይሆን ነበር፤ ግን አይደለም።

እግዚአብሔር በዚህ ምድር ላይ የሚያደርገውን ሁሉ በስውር የሚያደርግ አምላክ አይደለም። ቅዱሳት መጻሕፍትን ሰጥቶናል። በምዕ ራፍ ሁለት መጽሐፍ ቅዱስን ለምን እንደ እግዚአብሔር ቃል ማመን እንዳለብን የተወሰኑ ነጥቦችን አንሥቻለሁ። ስለዚህ ዐላማዬ እግዚአብ ሔር ምን ሊያደርግ እንደሚችል ቁጭ ብዬ በምናቤ ማሰብ አይደለም፤

ይልቁንም በቅዱሳት መጻሐፍት ውስጥ ቃሉን ማዳመጥና የምሰማው ንም ለእናንተ መምከር ነው እንጂ።

መንገዶቹ ምንኛ የማይመረመሩ ናቸው

እግዚአብሔር ምን እየሠራ ነው? የሚለውን ጥያቄ ከመመለሴ በፊት ሌላ ማለት ያለብኝ ነገር፣ እርሱ ሁልጊዜም ልናስተዉላቸው የማንችላቸውን በቢሊዮን የሚቈጠሩ ነገሮችን እንደሚሠራ ነው፦

“እግዚአብሔር አምላኬ ሆይ፤
አንተ ያደረግኸው ድንቅ ነገር ብዙ ነው፤
ለእኛ ያቀድኸውን፣
ሊዘረዝርልህ የሚችል ማንም የለም፤
ላውራው ልናገረው ብል፣
ስፍር ቍጥር አይኖረውም።” (መዝ. 40፥5)

በኮሮናቫይረስ ውስጥ ያለው የእርሱ ሐሳብ ከቍጥር በላይ ብቻ ሳይሆን፣ በብዙ መንገድ የማይመረመርም ጭምር ነው። “የእግዚአብሔር የጥበቡና የዕውቀቱ ባለጠግነት እንዴት ጥልቅ ነው! ፍርዱ አይመረ መርም፤ ለመንገዱም ፈለግ የለው” (ሮሜ 11፥33)። ጳውሎስ ይህን ሲል “በቃ መጽሐፍ ቅዱሳችሁን ዝጉትና የራሳችሁን እውነታ ፍጠሩ” ማለቱ አልነበረም።

በተቃራኒው ስለ እግዚአብሔር መንገድ በሰው ልጅ ውስን አኣምሮ ሊመረመር የማይቻል መሆኑ፣ በዓለም ላይ ስላለው ታላቅ ዜና

የዐሥራ አንዱ የሮሜ መጽሐፍ ምዕራፎች መደምደሚያና የከፍታ ጫፍ ተደርገው ተጽፈዋል። ሁሉም የተጻፈልን እንድንረዳው ነው። ለምሳሌ፣ ጳውሎስ የመከራ ክስተት የማይቀር መሆኑን ሲያስረዳ እንዲህ ይላል፦

> “በዚህ ብቻ ሳይሆን በመከራችንም ሐሤት እናደርጋለን፤ ምክን ያቱም መከራ ትዕግሥትን እንደሚያስገኝ እናውቃለን። ትዕግሥት ጽናትን፣ ጽናት የተፈተነ ባሕርይን፣ የተፈተነ ባሕርይ ተስፋን፣ ይህም ተስፋ ለዕፍረት አይዳርገንም፤ እግዚአብሔር በሰጠን በመ ንፈስ ቅዱስ ፍቅሩን በልባችን አፍስሶአልና።” (ሮሜ 5፥3-5)

“ማወቅ”! ቅዱሳት መጻሕፍት እግዚአብሔር የገለጠውን ነገር ጸን ድናውቅ ተጽፈዋል። በተለይ ደግሞ ስለ መከራ—የኮሮናቫይረስ ወረር ሽኝ ጭምር። ስለዚህ *የማይመረመር* ማለት እግዚአብሔር ሁል ጊዜ እኛ ከምናየው በላይ እየሠራ ነው ማለት ነው። የምናየውንም ቢሆን እርሱ ባይገልጥልን ኖሮ ባላየነው ነበር።

እውነታውን ማመልከት

ስለዚህ የእኔ ሥራ በታዋቂው የጆን ሌነን ሙዚቃ ውስጥ እንዳለው በምናብ ማሰብ አይደለም።[4] እርሱ ገነት እና ገሃነም እንደሌለና ሰማይን ብቻ እንድናስብ ይነግረንና እንደዚህ ዐይነት ነገርን ማሰብ በጣም ቀላል እንደ ሆነ ያስረዳናል። እስቲ ሞክሩት። ቀላል ነው፤ በጣም ቀላል። ኮሮናቫይረስ ቀላል ምናባዊ እይታ ሳይሆን ከበድ ያለ እውነታ ይፈል ጋል። እግዚአብሔርና ቃሉ በጣም የሚያስፈልጉን እውነታዎች ናቸው - እግሮቻችን የቆሙበት ዐለት። ስለዚህ ዐላማዬ ወደ እውነታው

ማመልከት እንጂ ዐዲስ እውነታን መፍጠር አይደለም። ዐላማዬ እግዚአ ብሔር የተናገረውን መስማትና ማጽናት እንጂ እንዲያው ምናባዊ ሐሳብ ማቅረብ አይደለም።

መጽሐፍ ቅዱስ ወደሚያስተምረው በማመልከት ከኮሮናቫይረስ ጋር አዛምዳለሁ። እናንተ ደግሞ ትክክል የሆነውን ፍረዱ።

ይህን ያልሁት ኢየሱስም "የአሁኑን ዘመን ስለ መመርመር" የተና ገረው ነገር ስለ ሆነ ነው። ሰዎች የአየር ጠባይን በመመርመር መረዳታ ቸው፣ ነገር ግን የእግዚአብሔርን መለኮታዊ ሥራ በታሪክ ውስጥ መመርመርና መረዳት ባለመቻላቸው ተቈጥቶ እንዲህ ብሎ ነበር፦

"እናንት ግብዞች፤ የምድሩንና የሰማዩን መልክ መመርመር ታውቁ በታላችሁ፤ ታዲያ ይህን የአሁኑን ዘመን መመርመር እንዴት ተሳና ችሁ? ታዲያ ራሳችሁ ትክክለኛ የሆነውን ነገር ለምን አትፈር ዱም?" (ሉቃ. 12፥56-57)

ስለዚህ የእግዚአብሔርን ርዳታ እንደምትጠይቁ፣ ወደ እግዚአብ ሔርም ቃል እንደምትመለከቱና ለራሳችሁ መርምራችሁ ትክክል የሆነውን እንደምትፈርዱ ተስፋ አደርጋለሁ። የምለውን በቅዱሳት መጻ ሕፍት እንደምትፈትኑ (1ዮሐ. 4፥1) እና መልካም የሆነውንም እንደ ምትይዙ (1ተሰ. 5፥21) ተስፋ አደርጋለሁ።

መከተል የሚገባን ስድስት መንገዶች

እግዚአብሔር በኮሮናቫይረስ ምን እያደረገ ነው ለሚለው ጥያቄ ለምሰጣቸው ለእያንዳንዱ ምላሾች ብዙ ገጾች ሊጻፉ ይችላሉ። ነገር ግን

ከሁኔታው አስቸኳይነት አንጻር ብዙ ጊዜ አልወስድም። ይህን መጽሐፍ ከዘጋችሁ በኋላ ልትከተሏቸው ትችላላችሁ ብዬ ያሰብኳቸውን የመጽሐፍ ቅዱስ እውነተኛ መንገዶችን ብቻ አመለክታችኋለሁ። ዐብረን በእያንዳንዱ መንገዱ ብንጓዝ ምንኛ ደስ ባለኝ፤ ሆኖም ግን ይህን ለእናንተ እተወዋለሁ። እግዚአብሔር ይምራችሁ።

እግዚአብሔር በኮሮናቫይረስ ምን እየሠራ ነው?

ምዕራፍ 6

ሞራላዊ ክፋትን ማሳየት

መልስ 1

እግዚአብሔር እንደ ሌሎቹ መቅሠፍቶች ሁሉ
በኮሮናቫይረስ ወረርሽኝም ዓለም ምን ያኽል ሞራላዊ ክፋትና
እግዚአብሔርን የማቃለል አሰቀያሚ ኃጢአት ውስጥ
እንዳለች በተጨባጭ መንገድ እያሳየ ነው።

በርግጥ ኃጢአት ለሁሉም አካላዊ ችግርና መከራዎች ምክንያት ነው። ሦስተኛው የመጽሐፍ ቅዱስ ምዕራፍ ኃጢአት እንዴት ወደ ዓለም እንደ ገባ ያስረዳል። ይህ ኃጢአት ለዓለም ዐቀፋዊ ጥፋትና ችግር ምንጭ መሆኑን ያሳያል (ዘፍ. 3፥1-19)። ሮሜ 5፥12 ላይ ጳውሎስ ሲጠቀልለው፡- “ስለዚህ ኃጢአት በአንድ ሰው በኩል ወደ ዓለም እንደ ገባ ሁሉ፣ ሞትም በኃጢአት በኩል ገብቶአልና፤ በዚሁ መንገድ ሞት ወደ ሰዎች ሁሉ መጣ፤ ምክንያቱም ሁሉም ኃጢአትን ሠርተዋልና፤” ይላል።

ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ዓለም ተሰብሯል። ውበቱ ሁሉ በክፋት፣ በአደጋዎች፣ በበሽታዎች እና ተስፋ በመቁረጥ ተጠላልፏል። እግዚአብሔር ፍጹም አድርጎ ፈጥሮት ነበር። “እግዚአብሔርም ያደረገውን ሁሉ አየ፤ እነሆም፣ እጅግ መልካም ነበረ።” (ዘፍ. 1፥31)። ነገር ግን ሰው በኃጢአት ከወደቀበት ከዚያ ቀን ጀምሮ፣ ታሪክ በአስገራሚ መልኩ ሙታን የሚጓዝበት የሚሽከረከር ቀበቶ (ቺንጋ) ሆነ።

ውድቀት ፍርድ ነው

መጽሐፍ ቅዱስ ይህን ስብራት በኃጢአት ለተሞላ ዓለም የእግዚአብሔር ፍርድ እንደ ሆነ እንጂ ተፈጥሮአዊ አድርጎ አይመለከተውም። ጳውሎስ በኃጢአት ምክንያት የመጣውን የእግዚአብሔር ፍርድ ውጤት ሲያብራራ እንዲህ ይላል፦

> “ፍጥረት ሁሉ ለከንቱነት ተዳርጎአልና፤ ይኸውም በራሱ ምርጫ ሳይሆን፣ ለተስፋ እንዲገዛ ካደረገው ከፈቃዱ የተነሣ ነው። ይህም ፍጥረት ራሱ ከመበስበስ ባርነት ነጻ ወጥቶ ለእግዚአብሔር ልጆች ወደ ሆነው ወደ ከበረው ነጻነት እንዲደርስ ነው። እስከ አሁን ድረስ ፍጥረት ሁሉ በምጥ ጊዜ እንዳለው ሥቃይ በመቃተት ላይ እንደሚገኝ እናውቃለን።” (ሮሜ 8፥20-22)

ከንቱነት፣ የመበስበስ ባርነት እና የሥቃይ መቃተት ይህች ዓለም ኃጢአት ወደ እርሷ ከመጣ በኋላ ምን ዐይነት የጥፋትና የክፋት መልክ እንዳላት ያሳያሉ። ጳውሎስ ይህም የእግዚአብሔር ፍርድ ውጤት እንደ ሆነ ተናግሯል፦ “ፍጥረት ሁሉ ለከንቱነት *ተዳርጎአልና፤* . . . ለተስፋ *እንዲገዛ* ካደረገው ከፈቃዱ የተነሣ ነው።” ሰይጣን ለተስፋ እንዲገዛ

አላደረገውም፤ አዳም ለተስፋ እንዲገዛ አላደረገውም፤ እግዚአብሔር ግን አድርጎታል። ጳውሎስ በሮሜ 5፥16 ላይ “ፍርዱ የአንድን ሰው ኃጢአት ተከትሎ ኵነኔን አመጣ” ይላል።

ልጆቹም ሳይቀሩ ከፍርድ በታች

ርግጠኛ ለመሆን ይህ ክፍል በተስፋ የተሞላ ነው - “ለእግዚአብሔር ልጆች ወደ ሆነው ወደ ከበረው ነጻነት እንዲደርስ ነው” (ሮሜ 8፥21)። እግዚአብሔር ለዐዲስ ፍጥረት አስደናቂ ዕቅድ አለው። ይህም “እንባን ሁሉ ከዐይናቸው ያብሳል” (ራእ. 21፥4) የሚለው ነው። ለአሁን ግን ሁላችንም ከፍርዱ በታች ነን፤ ምክንያቱም ዓለምን ለሞት፣ ለአደጋና ለችግር ዳርጓታል።

አዎን! የገዛ ልጆቹ የሆንን እኛ፣ ልጆቹ እንሆን ዘንድ አስቀድሞ የወሰነን (ኤፌ. 1፥5)፣ በደሙ በተደረገ ቤዛነት፣ የኃጢአትን ይቅርታ ያገኘን (ኤፌ. 1፥17)፤ ከቡር ለሆነው ለርስቱ ባለጠግነት ተስፋ የተጠራን (ኤፌ. 1፥18) በመከራና በሞት መካከል እናልፋለን፤ ምክንያቱም ይህ በውድቀት ላይ የሆነ የእግዚአብሔር ፍርድ ነው። “የመጀመሪያ ውን የመንፈስ ፍሬ ያገኘን እኛ ራሳችን የሰውነታችን ቤዛ የሆነውን ልጅነታችንን በናፍቆት እየተጠባበቅን በውስጣችን እንቃትታለን።” (ሮሜ 8፥23)። ክርስቲያኖች በሱናሚ ሕይወታቸውን ዐጥተዋል፤ በሽብርተኞች ተገድለዋል፤ በኮሮናቫይረስም ይጠቃሉ።

መቅጣት ሳይሆን ማንጻት

ክርስቶስን እጅግ ውድ ሀብታችን አድርገን ለተቀበልን ለእኛ ለክርስቲያኖች በዚህ ብልሹ ዓለም ውስጥ ማለፋችን ኾነኔ አለመሆኑ ልዩነታችን ነው። “ስለዚህ በክርስቶስ ኢየሱስ ያሉት አሁን ኾነኔ የለባቸውም” (ሮሜ 8፥1)። ለእኛ ይህ ሕመም የሚያነጻ እንጂ ቅጣት አይደለም።

“እግዚአብሔር ለቍጣ ወስኖ አላስቀመጠንም (1ተሰ. 5፥9)። ልክ እንደ ሌሎች ሰዎች ሁሉ በሕመምና በአደጋ እንሞታለን፤ ሆኖም ግን በክርስቶስ ለሆንን የሞት “መንደፊያ” ተወግዷል (1ቆሮ. 15፥55)። “ሞትም ማትረፍ ነው” (ፊል. 1፥21)። መሄድ ከክርስቶስ ጋር መሆን ነው (ፊል. 1፥23)።

ሰይጣን በእርግጥ ያለ እና የተገደበ ነው

የዚህን ዓለም መከራ ከእግዚአብሔር ፍርድ ጋር ሳያይዝ፣ ሰይጣን በዚህ ዓለም በሚገጥመን መከራ በከፍተኛ ደረጃ እንደሚሳተፍ እየካድ ሁኝ አይደለም። መጽሐፍ ቅዱስ ሰይጣንን “የዚህ ዓለም አምላክ” (2ቆሮ. 4፥4)፣ “የዚህም ዓለም ገዥ” (ዮሐ. 12፥31)፣ “በአየር ላይ ላሉት መንፈሳውያን ኀይላት ገዥ” (ኤፌ. 2፥2) ብሎ ይጠራዋል። “እርሱ ከመጀመሪያ ነፍሰ ገዳይ ነበር” (ዮሐ. 8፥44)። በብዙ በሽታዎች ያስራል፤ ያስጨንቃልም (ሉቃ. 13፥16፤ ሐ.ሥ. 10፥38)።

ሆኖም ግን ሰይጣን በልጓም የተያዘ ነው። ልጓሙም በእግዚአብሔር እጅ ነው። ያለ እግዚአብሔር ፈቃድ አይሠራም። በፈቃድና በገደብ

ብቻ ይሠራል (ኢዮ. 1፥12፤ 2፥6፤ ሉቃ. 22፥31፤ 2ቆሮ. 12፥7)። ሰይጣን የሚያደርሰውን የጉዳት መጠን የሚወስነው እግዚአብሔር ነው። ባያውቀውም የእግዚአብሔርን ፍርድ ያገለግላል እንጂ ከፍርዱ የተለየ አይደለም።

ቍልፍ ጥያቄ

አሁን የኮሮናቫይረስ ትርጕም ላይ እንድናተኵር የሚያደርገን ጥያቄ ላይ ደርሰናል። ለምንድነው እግዚአብሔር በሞራል(ግብረገብ) ክፋት ምክንያት አካላዊ ፍርድን ወደ ዓለም ያመጣው? አዳምና ሔዋን በእግዚአብሔር ላይ ዐመፁ፤ ልባቸውም ከእግዚአብሔር ዘወር አለ። ከእርሱ ይልቅ የራሳቸውን ጥቡብ፣ ከመተማመንም ይልቅ ነጻነትን መረጡ። ይህ ዐመፅና ምርጫ መንፈሳዊና ሞራላዊ ዐመፅ ነበር። በመጀመሪያ በአካል ሳይሆን በነፍስ፣ በሰው ላይ ሳይሆን በአምላክ ላይ የተደረገ ኃጢአት ነበር።

እግዚአብሔር ግን ለዚህ ሞራላዊና መንፈሳዊ ዐመፅ በምላሹ ይህን አካላዊውን ዓለም ለአዲጋና ለመከራ ዳረገ። ሁሉ ነገር የጀመረው ከነፍስ እንደ መሆኑ መጠን አዲጋንና መከራን ወደ ነፍስ አምጥቶ፣ ይህን ቁሳዊውን ዓለም በጥሩ ሁኔታ እንዲቀጥል ለምን አልተወውም?

መልስ

የእኔ አስተያየት እንዲህ ነው፦ እግዚአብሔር ቁሳዊውን ዓለም ከመርገም ሥር ከማድረጉ የተነሣ በበሽታና በመቅሠፍት የምናየው አካላዊ ጉስቍልና ኃጢአት ምን ያኽል አሰቃቂ እንደ ሆነ የሚያሳይ ስለ

ሆነ ነው። በሌላ አገላለጽ፣ *ለአካላዊ ክፉት* በእግዚአብሔር *ላይ የማመፅ ምራላዊ (ግብረገባዊ) ቍጣን የሚያሳይ ምሳሌ፣ ተውኔት ወይም ምልክት ነው።*

ይህ ለምን ተገቢ ሊሆን ይችላል? ኀጢአት ባሳወረውና ከውድቀት በኋላ ባለን በአሁኑ ማንነታችን በእግዚአብሔር ላይ ኀጢአት ማድረግ ምን ያክል አጸያፊ እንደ ሆነ ማየትም መረዳትም አንችልም። በዓለም ላይ ያለ ማንኛውም ሰው ከእግዚአብሔር በላይ ሌሎች ነገሮችን የመም ረጥን አሰቃቂነት መረዳት ያዳግተዋል። ለእግዚአብሔር ባለን ዕለታዊ ቸልተኛነትና እንቢተኛነት ተጨንቆ እንቅልፉን የሚያጣ ማን አለ?

ነገር ግን አካላዊ ሕመማችን ምን ያክል ይሰማናል! እግዚአብሔር ሰውነታችንን ቢነካ ምንኛ ልንበሳጭ እንችላለን! እግዚአብሔርን በልባ ችን ዝቅ በምናደርግበት መንገድ ግን ላናዝን እንችላለን። ሆኖም ኮሮና ቫይረስ ሲመጣና ሰውነታችንንም ሲያስፈራራ፣ እግዚአብሔር ትኵረታ ችንን ያነኛል። *ለአካላዊ ሕመም በዓለም ውሰጥ በጣም የተሳሳተ ነገር መኖሩን የሚናገር የእግዚአብሔር መለከት ነው።* በሽታና የአካል ጐደሎ ነት፣ ኃጢአት በመንፈሳዊ ዓለም ምን እንደሚመስል እግዚአብሔር በአካላዊ ዓለም የሚያሳይበት ምስል ነው።

ምንም እንኳ በምድር ያሉ ብዙ የእግዚአብሔር ሰዎችም ሕመምና የአካል ጐደሎነት ቢኖርባቸውም ይህ ግን እውነት ነው። መቅሠፍቶች ኃጢአት የሚገባውና፣ አንድ ቀን በብዙ ዕጥፍ በከፋ ፍርድ የሚቀበለው ምን እንደ ሆነ የሚያሳዩ ቅድመ ምልክታዎች እና ማስጠንቀቂያዎች ናቸው። በእግዚአብሔር ላይ የተደረገውን የሞራል ጥሰትና የመንፈሳዊ

ኅጢአት ገጽታን አስቀያሚነት እንድናይ የሚያደርጉ የማንቂያ ደወሎች ናቸው።

በእጆቹ ያበጃጀንን በንቀት፣ በቸልተኛነት፣ ባለማመን፣ ዝቅ በማድ ረግና ለጠጉራችን አሠራር ከምንሰጠው ትኵረት ያነሰ በልባችን ለእርሱ ትኵረት በመስጠት ማስተናገድ ምን ያኽል አሳፋሪ፣ አስከፊና አስጸያፊ እንደ ሆነ እኛ ሁላችን እንድናይና እንዲሰማን በሆነ ኖሮ።

ይህን ማየት አለብን፤ ይህ ሊሰማን ይገባል፤ አለዚያ ከአስቀያሚው ኅጢአት ደኅንነትን ፍለጋ ወደ ክርስቶስ ዘወር አንልም። ከኅጢአት ቅጣት ለማምለጥ ልንጮኽ እንችል ይሆናል፤ ነገር ግን እግዚአብሔርን የመናቅ፣ ያለማክበር ኅጢአትን፣ ሞራላዊ አስቀያሚነትን በውስጣችን አይተን ልንጠላው እንችላለንን? ይህን ካላደረግን፣ ያላደረግነው እግዚ አብሔር በኮሮናቫይረስ ዐይነት አካላዊ መከራ ውስጥ ግልጽ ምስልን ካለማሳየቱ የተነሣ አይደለም። ስለዚህ፣ እግዚአብሔር በዚህ ጊዜ በምሕ ረት ወደ እኛ እንዲህ በማለት እየጮኸ ነው፡- ንቁ! በእግዚአብሔር ፊት ኃጢአት ልክ እንደዚሁ ነው! አሰቃቂና የሚያስጠላ። ከኮሮናቫይረስም እጅግ በብዙ ዕጥፍ የከፋ ነው።

ምዕራፍ 7

ተገቢ መለኮታዊ ፍርድን መላክ

መልስ 2

ለንዳንድ ሰዎች በኮሮናቫይረስ የሚጠቁት በኃጢአት
ስለተሞላው አመለካከታቸውና ድርጊታቸው
ከእግዚአብሔር ዘንድ ስለ ተፈረደባቸው ነው።

የሁሉም መከራዎች ምንጭ እግዚአብሔርን ያለማክበር ኀጢአት ወደ ዓለም በመግባቱ ምክንያት የተከሠተው ውድቀት ነው ማለት እያንዳንዱ ሰው እያለፈበት ያለው መከራ ስለ ግል ኀጢአቱ የሚቀበለው ፍርድ ነው ማለት አይደለም። ለምሳሌ የኢዮብ መከራ ከራሱ ኀጢአት ጋር የሚገናኝ አልነበረም። የመጽሐፉ የመጀመሪያው ዐረፍተ ነገር ይህን ነገር ግልጽ ያደርገዋል፦ “ኢዮብ ... ነቀፋ የሌለበት፣ ቅን፣ እግዚአብሔርን የሚፈራና ከክፉት የራቀ ነበር።” (ኢዮብ 1፥1)።

ቀደም ብለን እንዳየነው የእግዚአብሔርም ሕዝብ የፍርዱ አብዛኛው አካላዊ ውጤት ያገኘዋል። ሐዋርያው ጴጥሮስ በዚህ መልክ ያስቀምጠዋል፦

> “ፍርድ ከእግዚአብሔር ቤት የሚጀምርበት ጊዜ ደርሶአልና። እን ግዲህ ፍርድ የሚጀምረው በእኛ ከሆነ ለእግዚአብሔር ወንጌል የማይታዘዙ ሰዎች መጨረሻቸው ምን ይሆን? እንግዲህ፣ “ጻድቅ የሚድነው በጭንቅ ከሆነ፣ ዐመፀኛውና ኀጢአተኛው እንዴት ሊሆን ይሆን?” (1ጴጥ. 4፥17-18)

“ከእግዚአብሔር ቤት” የሚጀምረው ፍርድ የሚያነጻ እንጂ የሚ ቀጣ አይደለም። ስለዚህ ሥቃዮች ሁሉ በተለዩ ኀጢአቶች ላይ የሚመጡ የተለዩ የእግዚአብሔር ፍርዶች አይደሉም። ሆኖም ግን እግዚአብሔር አንዳንድ ጊዜ እርሱን አሻፈረኝ ላሉና ራሳቸውን ለኃጢ አት በሚሰጡት ላይ የተወሰነ ፍርድን ለማምጣት በሽታን ይጠቀማል።

ምሳሌዎች፦ ለተወሰኑ ኀጢአቶች የተወሰኑ ፍርዶች

ለተወሰኑ ኀጢአቶች የተወሰኑ ፍርዶችን ለማሳየት ሁለት ምሳሌዎ ችን እሰጣችኋለሁ።

በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 12 ላይ ንጉሥ ሄሮድስ ራሱን አምላክ ተብሎ እንዲጠራ በመፍቀዱ ራሱን ከፍ ከፍ አደረገ። “ሄሮድስም ለእግ ዚአብሔር ክብር ስላልሰጠ የጌታ መልአክ ወዲያው መታው፤ በትልም ተበልቶ ሞተ።” (ሐ.ሥ. 12፥23)። እግዚአብሔር ራሳቸውን ከፍ ከፍ በሚያደርጉ ሁሉ ላይ ይህን ሊያደርግ ይችላል። ይህ ማለት የአብዛኞ

ቻችን ገዦች በእግዚአብሔርና በሰው ፊት ስለሚያሳዩት እብሪት በየቀኑ በሞት ባለ መመታታቸው ልንደነቅ ይገባል። የእግዚአብሔር ከማጥፋት መታቀብ ታላቅ ምሕረት ነውና።

ሌላው ምሳሌ ደግሞ የግብረ ሰዶማውያን ኀጢአት ነው። በሮሜ 1፥27 ላይ ሐዋርያው ጳውሎስ እንዲህ ይላል፦ “ወንዶች ለባሕርያቸው የሚገባውን ሴቶችን መገናኘት ትተው እርስ በርሳቸው በፍትወት ተቃጠሉ፤ ወንዶች ከወንዶች ጋር ነውር ፈጸሙ፤ ለክፉ አድራጎታቸው የሚገባቸውን ቅጣት በገዛ ራሳቸው ላይ አመጡ።” “በገዛ ራሳቸው” ላይ ያመጡት “የሚገባቸው ቅጣት” የኀጢአታቸው ክፉ ውጤት ነው።

ይህ “የሚገባቸው ቅጣት” በሮሜ 1፥18 ላይ ለምናየው የእግዚአብሔር ፍርድ አንድ ምሳሌ ነው። ክፍሉ እንዲህ ይላል፦ “በክፋታቸው እውነትን ዐፍነው በሚይዙ፣ በዐመፃቸውና በክፋታቸው ሁሉ ላይ የእግዚአብሔር ቍጣ ከሰማይ ይገለጣልና።” ስለዚህ ሁሉም መከራዎች ለተለያዩ ኀጢአቶች የተወሰኑ ፍርድ አይደሉም፤ አንዳንዶቹ ግን ናቸው።

ሁሉም ራሱን ይመርምር

ኮሮናቫይረስ በማንኛውም ሰው ላይ ግልጽና ቀላል ቅጣት አይደለም። የፍቅር ማንነት ያለውና በመንፈስ የተሞላ፣ ኀጢአቱም በክርስቶስ ይቅር የተባለለት ሰው በኮሮናቫይረስ ተይዞ ሊሞት ይችላል። ሆኖም መከራችን በአኗኗራችን ላይ የእግዚአብሔር ፍርድ ከሆነ እንድናስተውል እያንዳንዳችን ልባችንን መመርመራችን ተገቢ ነው።

ወደ ክርስቶስ ከመጣን፣ መከራችን የእግዚአብሔር የቅጣት ፍርድ እንዳይደለ ማወቅ እንችላለን። ይህን ማወቅ የቻልነው ኢየሱስ፡- “ቃሌን የሚሰማ፣ በላከኝም የሚያምን የዘላለም ሕይወት አለው፤ ከሞት ወደ ሕይወት ተሻገረ እንጂ ወደ ፍርድ አይመጣም።” (ዮሐ. 5፥24) ስላለ ነው። በክርስቶስ ኢየሱስ ያሉት ኵነኔ የለባቸውም (ሮሜ 8፥1)። ተግሣጽ እንጂ ጨርሶ ማጥፋት አይደለም። “ምክንያቱም ጌታ የሚወደውን ይገሥጻልና፤ እንደ ልጅ የሚቀበለውንም ይቀጣል።” (ዕብ. 12፥6)።

ምዕራፍ 8

ለዳግም ምጽአት ያነቃናል

መልስ 3

ኮሮናቫይረስ ለክርስቶስ ዳግም ምጽአት ዝግጁ እንድንሆን ከእግዚአብሔር የተሰጠ የማንቂያ ደወል ነው።

ምንም እንኳ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ስለ ዓለም መጨረሻ ተነግረው ነገር ግን ሳይፈጸሙ በቀሩ ትንበያዎች የተበከለ ቢሆንም፤ የኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም መምጣት እውነት እንደ ሆነ አለ። “እናንት የገሊላ ሰዎች ሆይ፤ ወደ ሰማይ እየተመለከታችሁ እዚህ የቆማችሁት ለምንድን ነው? ይህ ከእናንተ ዘንድ ወደ ሰማይ ሲያርግ ያያችሁት ኢየሱስ፣ ልክ ወደ ሰማይ ሲወጣ እንዳያችሁት በዚሁ ሁኔታ ይመለሳል” (ሐ.ሥ. 1፥11)።

በሚመጣም ጊዜ በዚህ ዓለም ላይ ይፈርዳል፦

“የሰው ልጅ ከመላእክቱ ሁሉ ጋር በክብሩ ሲመጣ፣ በክብሩ ዙፋን ላይ ይቀመጣል፤ ሕዝቦች ሁሉ በፊቱ ይሰበሰባሉ፤ እር ሱም፣ እረኛ በጎችን ከፍየሎች እንደሚለይ፣ ሕዝቡን አንዱን ከሌላው ይለያል፤ (ማቴ. 25፥31-32)። ”

ክርስቶስን ለመገናኘት ዝግጁ ላልሆኑ ሰዎች፣ ያ ቀን እንደ ወጥመድ በድንገት ይመጣባቸዋል፦

“እንግዲህ በገደብ የለሽ ሕይወት፣ በመጠጥ ብዛትና ስለ ኑሮ በመጨነቅ ልባችሁ እንዳይዝልና ያ ቀን እንደ ወጥመድ ድንገት እንዳይደርስባችሁ ተጠንቀቁ፤” (ሉቃ. 21፥34)።

የምጥ ጣር

ኢየሱስ እንደ ጦርነት፣ ራብና የመሬት መንቀጥቀጥ ያሉ ነገሮች ዳግም መምጣቱን እንደሚያመለክቱ ተናግሯል (ማቴ. 24፥7)። እነዚህ ንም ምልክቶች “የምጥ መጀመሪያ” ብሎ ጠርቷቸዋል (ማቴ. 24፥8)። ይህም ምስል፣ ምድርን ኢየሱስ በሚመጣበት ጊዜ የሚያመጣውን ዐዲሱን ዓለም ለመውለድ በመሞከር እያማጣች ያለችን ሴት ያስመስ ላታል።

ጳውሎስ በሮሜ 8፥22 ላይ ይህን ምስል በማንሣት የአሁን ዘመን የሥቃይ መቃተትን (አደጋና እንደ ኮሮናቫይረስ ያሉ ሕመሞችን) እንደ ምጥ ሥቃይ ይገልጻቸዋል። እኛንም በሕመሞቻችን የዚህች ዓለም

የምጥ ሥቃይ አካል አድርጎ ይሥለናል። ነገር ግን ሙታንን ሊያስነሣ እና የከበረና ዐዲስ ሥጋን ሊሰጠን የሚመጣውን ኢየሱስን (ፊል. 3፥21)፣ በመምጣቱ የምናገኘውን የሰውነታችንን ቤዛነት እየጠበቅን እንቃት ታለን፡-

> “ይህም ፍጥረት ራሱ ከመበስበስ ባርነት ነጻ ወጥቶ ለእግዚአ ብሔር ልጆች ወደ ሆነው ወደ ከበረው ነጻነት እንዲደርስ ነው። እስከ አሁን ድረስ ፍጥረት ሁሉ በምጥ ጊዜ እንዳለው ሥቃይ በመቃተት ላይ እንደሚገኝ እናውቃለን። እርሱ ብቻ ሳይሆን፣ የመጀመሪያውን የመንፈስ ፍሬ ያገኘን እኛ ራሳችን የሰውነታችን ቤዛ የሆነውን ልጅነታችንን በናፍቆት እየተጠባበቅን በውስጣችን እንቃትታለን። (ሮሜ 8፥21-23)

ንቁ!

እያልኩኝ ያለሁት እንዲህ ነው፡- ኢየሱስ የምጥ ጣር መጀመሪያዎች (ኮሮናቫይረስን ጨምሮ) እርሱ እንደሚመጣና እኛም መዘጋጀት እንደ ሚያስፈልገን ማንቂያና ማስታወሻ መሆናቸውን እንድናስተውል ይሻል። “የሰው ልጅም ባላሰባችሁት ሰዓት ይመጣልና እናንተም እንደዚሁ ዝግጁ ሁኑ።” (ማቴ. 24፥44)።

ኢየሱስ የተናገረውን በቁም ነገር ለመመልከት የሚመጣበትን ቀን ተንባዮች መሆን አይጠበቅብንም። እርሱ የሚናገረው ስሕተት የሌለው ነውና። “ስለዚህ ጊዜው መቼ እንደሚሆን አታውቁምና ተጠንቀቁ፤

ትጉ፥... እንግዲህ የቤቱ ባለቤት... መቼ እንደሚመጣ አታውቁምና ተግታችሁ ጠብቁ፤...ለእናንተ የምነግራችሁን ለሰው ሁሉ እናገራለሁ፤ ተግታችሁ ጠብቁ!" (ማር. 13፥33-37)

መልእክቱ ግልጽ ነው፡- ተግታችሁ ጠብቁ! ተግታችሁ ጠብቁ! ተግታችሁ ጠብቁ! የዚህ ዓለም የምጥ ጣሮች ለዚህ መልእክት የሚውሉ ናቸው። ኦ! ምን ያህል ሰው ግን ትጋት ይጎለዋል! ለሥራዎቻቸው ሁሉ ዕረፍት ዐጥተው ስለ ክርስቶስ ዳግም መምጣት ግን ለጥ ብለው ተኝተዋል። የዚህ አደጋው እጅግ ትልቅ ነው፤ ኮሮናቫይረስ ግን ተዘጋጅተን እንድንጠብቅ የምሕረት ማንቂያ ደወል ነው።

ተዘጋጅቶ መጠበቅ ማለት ወደ ክርስቶስ መምጣት፣ ለኃጢአት ይቅርታን መቀበልና በእርሱ ብርሃን መመላለስ ነው። ከዚያ በኋላ የሚከተለው ከተነገረላቸው ሰዎች አንዱ እንሆናለን፡-

> "እናንተ ግን ይህ ቀን እንደ ሌባ ያስደነግጣችሁ ዘንድ በጨለማ ውስጥ አይደላችሁም፤ ሁላችሁም የብርሃን ልጆች፣ የቀንም ልጆች ናችሁና።... እንግዲህ እንንቃ፤... እግዚአብሔር ድነትን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ አማካይነት እንድናገኝ ነው እንጂ ለቍጣ ወስኖ አላስቀመጠንምና። ብንነቃም ሆነ ብናንቀላፋ ከእርሱ ጋር በሕይወት እንድንኖር እርሱ ስለ እኛ ሞተ።" (1ተሰ. 5፥4-10)።

ምዕራፍ 9

በእውነተኛ ንስሓ ራሳችንን ያለገደብ ለክርስቶስ መስጠት

መልስ 4

የኮሮናቫይረስ ለሁላችንም ንስሓ እንድንገባና ፣
ያለገደብ ሕይወታችንን ለክርስቶስ እንድንሰጥ
የሚያደርግ የእግዚአብሔር የማንቂያ ደወል ነው።

ኮሮናቫይረስ ለንስሓ የተደረገ ብቸኛው ጥሪ አይደለም። በርግጥ የትኞቹም ተፈጥሮአዊ አደጋዎች. . . ጐርፍ፣ ራብ፣ አንበጣ፣ ሱናሚ (የውቅያኖስ ውሃ ማጥለቅለቅ) ወይም በሽታ ቢያሠቃዩም፣ በምሕረት የተሞሉ ወደ ንስሓ የሚመሩን የእግዚአብሔር ጥሪዎች ናቸው።

ኢየሱስ በሉቃስ 13፥1-5 ባለው ክፍል ውስጥ ለተፈጠረ አደጋ ከሰጠው ምላሽ ይህን እናያለን፦

በዚህ ጊዜ መጥተው፣ ጲላጦስ ደማቸውን ከመሥዋዕታቸው ጋር ስለ ደባለቀው ስለ ገሊላ ሰዎች ያወሩለት ሰዎች በዚያ ነበሩ። እርሱም እንዲህ መለሰላቸው፤ “ታዲያ እነዚህ የገሊላ ሰዎች ይህ ሥቃይ የደረሰባቸው ከሌሎቹ የገሊላ ሰዎች ሁሉ ይልቅ ኀጢአተኞች ስለ ነበሩ ይመስላችኋል? አይደለም፤ እላችኋለሁ፤ ንስሓ ካልገባችሁ ሁላችሁ እንደዚሁ ትጠፋላችሁ። ወይም ደግሞ በሰሊሆም ግንብ ተንዶባቸው የሞቱት ዐሥራ ስምንት ሰዎች በኢየሩሳሌም ከሚኖሩት ሰዎች ሁሉ ይልቅ በደለኞች ስለ ነበሩ ይመስላችኋል? አይደለም፤ እላችኋለሁ፤ ንስሓ ካልገባችሁ ሁላችሁ እንደዚሁ ትጠፋላችሁ።”

ጲላጦስ ሊያመልኩ ወደ ቤተ መቅደስ የሄዱትን ሰዎች በቤተ መቅደስ ገድሎ ነበር። በሰሊሆም ደግሞ ግንብ ተንዶ በአቅራቢያው የነበሩ ዐሥራ ስምንት ሰዎች ሞተው ነበር። አንደኛው አደጋ የሰው የመከፋት ፍሬ ሲሆን፤ ሌላው ደግሞ ድንገተኛ አደጋ እንደ ነበረ ግልጽ ነው።

የመቅሠፍት ትርጉም - ለእናንተ

ሰዎቹ “የዚህ ነገር ትርጉም ምንድነው? እግዚአብሔር ለየት ላለ ኃጢአት ያደረገው ልዩ ፍርድ ነውን?” ብለው ለሚያቀርቧቸው ጥያቄ ዎች ምላሽን ከኢየሱስ ፊልገው ነበር። የኢየሱስ መልስ ግን አስደናቂ ነው። በነዚህ አደጋዎች የሞቱትን ሰዎች ብቻ የሚመለከት ሳይሆን ለሁሉም ሰው የሚሆንን ትርጉም አወጣ። በሁለቱም ጉዳዮች

“በጲላጦስ የተገደሉትም ሆኑ ግንቡ የተደረመሰባቸው *ከእናንተ* በላይ የከፉ ኀጢአተኞች አልነበሩም።”

የእናንተ? ለምን የእነርሱን ኃጢአት ማንሣት አስፈለገው? ስለ ራሳቸው ኃጢአት የእርሱን አስተያየት እየጠየቁት አልነበረም። የእነርሱ ጉዳት ስለ ሌሎቹ ለማወቅ ነበር። ፍላጎታቸው አደጋው ለተጐጂዎቹ ምን ማለት እንደ ሆነ እንጂ ለተቀረነው ለእኛ ያለውን ትርጉም ለማወቅ አልነበረም።

ይህ ነው የኢየሱስን መልስ በጣም አስደናቂ የሚያደርገው። በመሠ ረቱ የእነዚህ አደጋዎች ትርጉም ለሁሉም ሰዎች ነው ማለቱ ነው። መልእክቱም “ንስሓ ግቡ አለዚያ ትጠፋላችሁ” የሚል ነው። ይህን ሁለት ጊዜ ብሎታል፦ “ንስሓ ካልገባችሁ ሁላችሁ እንደዚሁ ትጠፋ ላችሁ።” (ሉቃ. 13፥3)። “ንስሓ ካልገባችሁ ሁላችሁ እንደዚሁ ትጠፋ ላችሁ።” (ሉቃ. 13፥5)።

ጊዜ ሳለ የተደረገ የምሕረት ጥሪ

ኢየሱስ ምን እያደረገ ነበር? ሰዎቹ የተደነቁበትን አቅጣጫ እያስ ቀየረ ነበር። እነዚህ ሰዎች ኢየሱስን እንዲጠይቁ የገፋፋቸው መደነቅ በትክክለኛው አቅጣጫ ላይ አልነበረም። እነርሱን በጣም የደነቃቸው ሰዎች በጭካኔ መገደላቸውና ትርጉም የለሽ በሆነ መንገድ መሞታቸው ነበር። ኢየሱስ የሚነግራቸው ግን “ልትደነቁ የሚገባችሁ እናንተ ከተገደ ሉትና ከሞቱት አንዱ ባለመሆናችሁ ነው። በርግጥ ንስሓ ካልገባችሁ እናንተ ራሳችሁ እንደዚሁ ዐይነት ፍርድ አንድ ቀን ይገጥማችኋል።”

ከዚህ ክፍል፣ እግዚአብሔር በእንደዚህ ዐይነት በሽታዎች ውስጥ የምሕረት መልእክት እንዳለው ተረድቻለሁ። መልእክቱም ሁላችንም ኀጢአተኞች የሆንንና ለጥፋት የተዳረግን ስንሆን፣ አደጋዎች ደግሞ ጊዜ እያለ ንስሓ እንድንገባና እንድንድን ከእግዚአብሔር ዘንድ የሚደረጉ የጸጋ ጥሪዎች ናቸው። ኢየሱስ ጉዳዩን ከሞቱት በሕይወት ወዳሉት ቀይሮት ይህን አለ፦ “ይህ በጣም አስቸኳይ ነውና ስለ ሞቱት ሳይሆን በሕይወት ስላላችሁት ስለ እናንተ እናውራ። በእነርሱ ላይ የሆነው ነገር እናንተን ለማስጠንቀቅ ነው።የእናንተ ትልቁ ጉዳይ የእነርሱ ኃጢአት ሳይሆን የእናንተ ኃጢአት ነው።” ይህ በዚህ የኮሮናቫይረስ ወረርሽኝ ለዓለም የእግዚአብሔር መልእክት እንደ ሆነ ዐስባለሁ። እርሱ ገና ጊዜ ሳለ ዓለምን ወደ ንስሓ እየጠራት ነው።

ንስሓ ምን ማለት ነው?

የበለጠ ነገሩን ሰብሰብ አድርገን እንየው። ንስሓ ምን ማለት ነው? በዐዲስ ኪዳን ያለው ቃል የልብና የአእምሮ ለውጥ ማለት ነው። ላይ ላዩን የሆነ የአመለካከት ማሻሻያ ሳይሆን ጥልቅ በሆነ መንገድ በመለወጥ እግዚአብሔርና ኢየሱስ በእውነት ማን እንደ ሆኑ ማስተዋል ነው። ኢየሱስ ለውጡን እንዲህ ይገልጸዋል፦

> “ጌታ አምላክህን በፍጹም ልብህ፣ በፍጹም ነፍስህ፣ በፍጹም ሐሳብህ ውደድ፤” (ማቴ. 22፥37)

> “ከእኔ ይልቅ እናቱን ወይም አባቱን የሚወድ ለእኔ ሊሆን አይገባም፤ ከእኔ ይልቅ ወንድ ልጁን ወይም ሴት ልጁን የሚወድ ለእኔ ሊሆን አይገባም።” (ማቴ. 10፥37)

በሌላ አገላለጽ፣ ንስሓ የሚፈልገው ዋናው የልብና የአእምሮ ለውጥ፣ ባለን ማንነት ሁሉ እግዚአብሔርን መፈለግና፤ ከሌሎች ግንኙነ ቶቻችን ሁሉ በላይ ኢየሱስን መፈለግ ነው።

ለምን ኢየሱስ በጥፋት(በሞት) ያስፈራራናል?

ኢየሱስ እኛ ሁላችን ንስሓ ካልገባን እንዲሁ እንደምንጠፋ የተናገ ረበት ምክንያት፣ ሁላችንም እግዚአብሔር የሆነውን የከበረ ሀብት ከእርሱ ያነሰ ዋጋ ባላቸውና እኛ ግን አብልጠን በምንወዳቸው ነገሮች ስለቀየርን (ሮሜ 1፥22-23) እና ኢየሱስን ከገንዘብ፣ ከመዝናኛ እንዲ ሁም ከጓደኞቻችንና ከቤተ ሰቦቻችን ያነሰ አስፈላጊ አድርገን በመቁጠ ራችን ነው። እኛ ሁላችን ልንጠፋ የተገባን የሆንነው ከተላለፍናቸው የሕግ ዝርዝሮች አንጻር ሳይሆን የራሳችንን ገደብ የለሽ እሴቶች አክብረን እግዚአብሄር በክርስቶስ ኢየሱስ ለኛ የሰጠንን ገደብ የለሽ እሴቶች ስለ ናቅናቸው ወይንም ስላቃለልናቸው ነው።

እኛኑ በሚያጠፉን ምርጫዎቻችን ላይ መንቃት

ንስሓ ማለት ከወርቅ በላይ ቁርቁሮን፣ ከዐለት መሠረት በላይ አሸዋን ከመምረጥ ዐይነት ራስን የማጥፊያ ምርጫዎች መንቃት ነው። ሲ.ኤስ.ሉዊስ እንደ ጻፈው፡-

> እኛ፣ ልክ በባሕር አከባቢ የዕረፍት ጊዜን ማሳለፍ ምን እንደሚ መስል ማሰብ ስለማይችል መንደር ውስጥ በጭቃ እንደሚጫ ወት ሕፃን ልጅ፣ ገደብ የለሽ ደስታ ተሰጥቶን ሳለ በመጠጥ፣

በወሲብና በምኞት የምንሞኝ ግማሽ ልብ ያለን ፍጡራን ነን። በጣም በቀላሉ እንደሰታለን[5]።

ሉዊስ “ገደብ የለሽ ደስታ” የሚለው የክርስቶስን ውበት፣ ታላቅነት ና ዋጋን ማየት፣ ማጣጣምና ማካፈልን ነው።

በክርስቶስ ለመታመን መነሳት

እግዚአብሔር በኮሮናቫይረስ በኩል አሰቃቂ በሆነና፣ በሚያሠቃይ መንገድም ቢሆን በክርስቶስ ገደብ የለሽ ዋጋና ታላቅነት ያገኘነውን ደኅንነትና ርካታ ሊሰጠን የሚችል ሌላ ነገር እንደሌለ እያሳየን ነው። ይህ ዓለም ዐቀፍ ወረርሽኝ የመንቀሳቀስ ነጻነታችንን፣ የንግድ እንቅስቃሴዎ ቻችንን እና የፊት ለፊት ግንኙነታችንን ወስዶብናል። ደኅንነታችንን እና ምቾታችንንም ቀምቶናል። ምናልባት በመጨረሻም ሕይወታችንንም ይወስድ ይሆናል።

እግዚአብሔር ለእንደዚህ ዐይነት ኪሳራ ለሚመስል ሁኔታ ሲያጋ ልጠን በክርስቶስ ብቻ ለመታመን እንድንነሳ ነው። ይህን በሌላ መንገድ ለማስቀመጥ፦ የመከራ ጊዜን ክርስቶስን ለዓለም የማቅረቢያ ኢጋጣሚ የሚያደርገው ምክንያት ከሁሉ የበላይ የሆነውና በሁሉ አስደሳች የሆነው የክርስቶስ ታላቅነት፣ ክርስቶስ እኛን በመከራ ውስጥ በማጽናት ደስታን ሲያጎናጽፍ ለሌሎች በአንጻባራቂ ሁኔታ ስለሚያበራ ነው።

ተስፋ የመቁረጥ ስጦታ

እስቲ ዐስቡ፤ ለምሳሌ፤ እግዚአብሔር ለምን ጳውሎስን በሕይወት ተስፋ ወደሚቆርጥበት ደረጃ አመጣው?

“ወንድሞች ሆይ፤ በእስያ ስለ ደረሰብን መከራ እንድታውቁ እንወዳለን፤ በሕይወት ለመኖር እንኳ ተስፋ እስከምንቈርጥ ድረስ ከዐቅማችን በላይ የሆነ ጽኑ መከራ ደርሶብን ነበር። በርግጥም የሞት ፍርድ እንደ ተፈረደብን ይሰማን ነበር፤ ይህም የሆነው ሙታንን በሚያስነሣ በእግዚአብሔር እንድንታመን እንጂ፣ በራሳችን እንዳንታመን ነው።” (2ቆሮ. 1፥8-9)

ጳውሎስ ይህን ተስፋ የቈረጠበትን ኣጋጣሚ ሰይጣናዊ ወይም ደግሞ ድንገቴ አድርጎ አላየውም። ከዚህ ይልቅ ዐላማ እንዳለውና ያም ዐላማ የእግዚአብሔር እንደ ሆነ ነው የተጠቀሰው፡- “ይህም የሆነው ሙታንን በሚያስነሣ በእግዚአብሔር እንድንታመን እንጂ፣ በራሳችን እንዳንታመን ነው።” (1፥9)።

ይህ በኮሮናቫይረስ አማካኝነት የተላለፈ መልእክት ነው፡- በራሳችሁ መታመን አቁሙና ወደ እግዚአብሔር ዘወር በሉ። እናንተ ሞትን ማስቆም እንኳ አትችሉም፤ እግዚአብሔር ግን ሙታንን ማስነሣት ይችላል። በርግጥ “በእግዚአብሔር መታመን” ማለት ክርስቲያኖች ሥራ ፈት ናቸው ማለት አይደለም። ክርስቲያኖች ሥራ ፈት ሆነውም አያውቁም። ይልቁንስ የሥራችን መሠረት፣ አካሄድና እና ግብ እግዚአብሔር ነው ማለት ነው። ጳውሎስ “እንዲያውም ከሁሉም በላይ በትጋት ሠርቻለሁ፤ ዳሩ ግን እኔ ሳልሆን ከእኔ ጋር ያለው የእግዚአብሔር ጸጋ ነው።” (1ቆሮ. 15፥10) እንዳለው።

የኮሮናቫይረስ፣ እግዚአብሔርን በሕይወታችን በኹሉ አስፈላጊ፣ በሕይወታችን ተጨባጭ እውነታ እንድናደርገው ዘንድ ጥሪውን ያስተላ

ልፋል። ሕይወታችን የእስትንፋሳችን ጥገኛ ከሆነችው በላይ በእግዚ አብሔር ላይ ጥገኛ ናት። አንዳንዴ እኛን ወደ እርሱ ለመሳብ ትንፋሻች ንንም ይወስዳል።

የመውጊያ እሾህ ትርጉም

በጳውሎስ ሥጋ ላይ በነበረው የሚያሠቃይ መውጊያ የእግዚአብ ሔርን ዓላማ ምን እንደነበረ አስቡ፡-

> “ከዚህ ታላቅ መገለጥ የተነሣ እንዳልታበይ የሥጋዬ መውጊያ፣ እርሱም የሚያሠቃየኝ የሰይጣን መልእክተኛ ተሰጠኝ። ይህ ነገር ከእኔ እንዲወገድልኝ፣ ጌታን ሦስት ጊዜ ለመንሁት፤ እርሱ ግን፣ “ጸጋዬ ይበቃሃል፤ ኀይሌ ፍጹም የሚሆነው በድካም ጊዜ ነውና” አለኝ። ስለዚህ የክርስቶስ ኀይል በእኔ ያድር ዘንድ፣ ይበልጥ ደስ እያለኝ በድካሜ እመካለሁ።” (2ቆሮ. 12፥7-9)

ጳውሎስ በትልቅ መገለጥ ተባርኮ ነበር። እግዚአብሔር በመታበይ ውስጥ ያለውን አደጋ፣ ሰይጣን ደግሞ በእውነትና በደስታ ውስጥ ያለውን አደጋ አይተው ነበር። እግዚአብሔር የሰይጣንን ስልት ይገዛል፣ ስለሆነም ሰይጣን የጳውሎስን ምስክርነት የሚያበላሽ እየመሰለው የጳ ውሎስን ትሕትናና ደስታ በርግጥ እያገለገለ ነበር። ጳውሎስ በሰውነቱ መውጊያ አገኘ… የሰይጣን መልእክተኛን!… እንዲሁም የእግዚአብሔር መልእክተኛ! መውጊያው ምን እንደ ሆነ አናውቅም፤ ግን መውጊያ እንደ ሚያም እናውቃለን። ደግሞ ጳውሎስ ሦስት ጊዜ መወጊያውን ክርስቶስ እንዲያነሣለት ጠይቆም እንደ ነበር እናውቃለን።

ነገር ግን ክርስቶስ አላነሣለትም። ከዚህ ይልቅ በዚያው ሕመም ውስጥ ዐላማ ነበረው፣ እርሱም “ጎይሌ ፍጹም የሚሆነው በድካም ጊዜ ነውና” (2ቆሮ. 12፥9) የሚል ነበር። ዐላማው በጳውሎስ የማይለዋወጥ እምነትና ደስታ ውስጥ ክርስቶስ ከጤና ይልቅ እጅግ የከበረ መሆኑን ማንጸባረቅ ነው። ለዚህ ዐላማ የጳውሎስ ምላሽ “ይበልጥ ደስ እያለኝ በድካሜ እመካለሁ።” (2ቆሮ. 12፥9) የሚል ነበር።

ጳውሎስ ደስ እያለኝ! ሲል፣ ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል? መውጊያውን በደስታ ለመያዝ ለምን ፈቃደኛ ሆነ? ምክንያቱም የእርሱ ትልቁ ዐላማ በሕይወትም ሆነ በሞት ክርስቶስ በሥጋው እንዲከበር ስለሆነ (ፊል. 1፥20)። የጳውሎስ ደስታ የክርስቶስን ውበት ማየት፣ ክርስቶስን እንደ ውድ ሀብቱ ከፍ አድርጎ መያዝ እና ከጤናና ከሕይወት እንደሚሻል ክርስቶስን ለዓለም ማሳየት ነበር። በማርታ ስኔል ኒከልሰን (1898–1953) የተጻፈ “መውጊያው” የተሰኘ ቄንጆ ግጥም እንዲህ ይቋጫል፡-

> ያለተጨማሪ ጸጋ በጭራሽ መውጊያን ብቻ እንዳይሰጥ
> ተምሬአለሁ፣
> ፊቱ እንዳይደበቅ መሸፈኛን ዘወር ሊያደርግ መውጊያውን
> እንዲወስደውም ዐውቃለሁ።

በማጣት፣ ማግኘት

ጳውሎስ ማጣቱንም ይቀበላል፤ ምክንያቱም በማጣቱ ምክንያት ክርስቶስን በሙላት ያገኘዋልና፡-

“ከዚህም በላይ ለእርሱ ብዬ ሁሉን ነገር የተውሁለትን፣ ወደር የሌለውን ጌታዬን ክርስቶስ ኢየሱስን ከማወቅ ታላቅነት ጋር ሳነጻጽር፣ ሁሉንም ነገር እንደ ጉድለት እቈጥረዋለሁ፤ ለእርሱ ስል ሁሉን ዐጥቻለሁ፤ ክርስቶስን አገኝ ዘንድ ሁሉን እንደ ጉድፍ እቈጥራለሁ፤” (ፊል. 3፥8)

ንስሓ ማለት ይህ ነው፡- ከሕይወት በላይ በክርስቶስ እግዚአብሔርን የሚፈልግ የተለወጠ ልብና አእምሮን መለማመድ ነው። “ምሕረትህ ከሕይወት ይበልጣልና፤ ከንፈሮቼ ያመሰግኑሃል።” (መዝ. 63፥3)። ይህ የጳውሎስ እምነት ነበር። ይህ በሕይወትም ሆነ በሞት እውነት ነው። በሕይወት፣ ምክንያቱም ክርስቶስ ከሁሉም የሚበልጥ የሁሉም ደስታ ጣዕም ነውና። በሞት፣ ምክንያቱም “በአንተ ዘንድ የደስታ ሙላት፣ በቀኝህም የዘላለም ፍሥሓ አለና።” (መዝ. 16፥11)።

የኮሮናቫይረስ ወረርሽኝም በትንሹ ምኞትን ከማጣት እስከ ትልቁ ሕይወትን ማጣት በሚደርስ ማጣት የምናልፍበት ወቅት ነው። የጳውሎስን የደስታ ምስጢር ካወቅን ግን ማጣታችንን እንደ ማግኘት ልንቆጥረው እንችላለን። እግዚአብሔር ለዓለም እያለ ያለው ይህን ነው፡- በእውነተኛ ንስሓ ሁለንተናችንን (ራሳችንን) ለክርስቶስ እንስጥ።

ምዕራፍ 10

በኢደጋዎች መካከል መልካም ሥራዎችን መፍጠር

መልስ 5

ኮሮናቫይረስ እግዚአብሔር ለራሱ ሕዝብ፣ ያለበትን ለራሱ ቁጭ ብሎ ማዘንና ፍርሀትን በማሸነፍ፣ ብርታት በሞላው ደስታ እግዚአብሔርን የሚያከብር፣ ከፍቅር የመነጨ መልካም ሥራ እንዲሠራ ያደረገው ጥሪ ነው።

ኢየሱስ ተከታዮቹን እንዲህ ሲል አስተምሯል፣ “ሰዎች መልካሙን ሥራችሁን አይተው በሰማይ ያለውን አባታችሁን እንዲያ ከብሩ ብርሃናችሁ በሰዎች ፊት ይብራ።” (ማቴ. 5፥16)። ብዙውን ጊዜ የማይስተዋለው ነገር፣ በዚህ መንገድ የዓለም ብርሃን እና የምድር ጨው መሆን የበለጠ ብሩህ እና የበለጠ ጨዋማ እንደሚያደርግ ነው፤ ምክን ያቱም መልካም ሥራዎች በመከራ መካከል እንኳ መደረግ ስለ ነበረባቸው ነው።

በአደጋ ጽልመት ላይ ብርሃን

ኢየሱስ እንዲህ ብሎአል፡- “ሰዎች በእኔ ምክንያት ቢሰድቧችሁ፣ ቢያሳድዷችሁና ክፉውን ሁሉ በሐሰት ቢያስወሩባችሁ፤ ብፁዓን ናችሁ። በሰማይ የምትቀበሉት ዋጋ ታላቅ ስለ ሆነ ደስ ይበላችሁ፤ ሐሤት አድርጉ፤” (ማቴ. 5፥11-12)። ከዚያ በቀጥታ እንዲህ ወደ ማለት ዐለፈ፡- “እናንተ የምድር ጨው ናችሁ… የዓለም ብርሃን ናችሁ” (ማቴ. 5፥13-16)።

የክርስትና ድምቀትና መዐዛ መልካም ሥራ ብቻ ሳይሆን፣ በአደጋ መካከል የሚደረግ መልካም ሥራ ነው። ብዙ ክርስቲያን ያልሆኑ ሰዎች መልካም ሥራን ያደርጋሉ። ነገር ግን በእነርሱ ምክንያት ሰዎች እግዚአብሔርን እምብዛም አያከብሩም።

በርግጥ በማቴዎስ 5 ላይ ያለው አደጋ መሰደድ እንጂ በሽታ አይደለም። መሠረታዊ መርሑ ግን ተመሳሳይ ነው። በበሽታም ይሁን በመሰደድ ወቅት የሚደረጉ ከፍቅር የመነጩ መልካም ሥራዎች የሚያመለክቱት፣ ሥራዎቹ የተደገፉት በእግዚአብሔር ላይ ባለ ተስፋ የመሆኑን እውነታ ነው።

ለምሳሌ፣ ኢየሱስ እንዲህ አለ፡-

> “ነገር ግን ግብጥ ባዘጋጀህ ጊዜ ድኾችን፣ አካለ ስንኩሎችን፣ ሽባዎችንና ዐይነ ስውሮችን ጥራ፤ ትባረካለህም። እነዚህ ብድር ሊመልሱልህ ስለማይችሉ፣ በጻድቃንም ትንሣኤ ብድራትህ ይመለስልሃል።” (ሉቃ. 14፥13-14)

ከሞት ባሻገር (“በጻድቃንም ትንሣኤ ብድራትህ ይመለስልሃል”) በእግዚአብሔር ላይ ያለ ተስፋ በዚህ ሕይወት ውስጥ ሽልማትን የማይ ጠብቁ መልካም ሥራዎችን ያበረታታል፤ እንዲሁም ኀይልን ይሰጣል። ይህ ለአደጋ ለሚያጋልጡን በተለይም ለሞት ተጋላጭ ለሚያደርጉን መልካም ሥራዎችም ተመሳሳይ እውነት ነው።

ጴጥሮስ የኢየሱስን ትምህርት የተገበረበት መንገድ

ሐዋርያው ጴጥሮስ ከየትኛውም የዐዲስ ኪዳን ጸሓፊ በላይ ስለ መልካም ሥራዎች የኢየሱስን ግልጽ ትምህርት ያነሣል፦

> “ምንም እንኳ ክፉ እንደምትሠሩ አድርገው ቢያሚችሁም ለፍርድ በሚመጣበት ጊዜ መልካሙን ሥራችሁን አይተው እግዚአብሔርን እንዲያከብሩ፣ በአሕዛብ መካከል በመልካም ሕይወት ኑሩ።” (1ጴጥ. 2፥12)

በአደጋ ወቅት መልካም ስለ ማድረግም ጴጥሮስ ተመሳሳይ ነገር ተናግሯል። “ስለዚህ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ መከራ የሚቀበሉ ሁሉ ነፍሳቸውን ለታመነ ፈጣሪ ዐደራ ሰጥተው መልካም ማድረጋቸውን ይቀጥሉ።” (1ጴጥ. 4፥19) ይላል። በሌላ አነጋገር የመከራ መከሠት ዕድል ወይም እውነታ መልካም ሥራ ከመሥራት እንዲያቆማችሁ አትፍቀዱለት።

ክርስቶስ የሞተው በአደጋዎች ውስጥ መልካም ሥራን ለመፍጠር ነው።

ጴጥሮስ ይህን ዐዲስ ሕይወት ስለ ኀጢአታችን ከሆነው ከኢየሱስ ሞት ጋር ያገናኘዋል። “ለኃጢአት ሞተን ለጽድቅ እንድንኖር እርሱ

[ክርስቶስ] ራሱ በሥጋው ኀጢአታችንን በዕንጨት መስቀል ላይ ተሸከመ" (1ጴጥ. 2፥24)። ክርስቲያኖች ከክርስቶስ የተነሣ ኃጢአትን ገድለው ለጽድቅ መልካም ሥራዎች ራሳቸውን ያኖራሉ።

ጳውሎስ በኢየሱስ ሞት እና በክርስቲያኖች የመልካም ሥራ ትጋት መካከል ተመሳሳይ ግንኙነት ይፈጥራል፦ "እርሱም [ክርስቶስ] ከክፉት ሊቤዠን *መልካም የሆነውን ለማድረግ* የሚተጋውን የእርሱ የሆነውን ሕዝብ ለራሱ ያነጻ ዘንድ ራሱን ስለ እኛ ሰጥቶአል።"

በተጨማሪም ጳውሎስ ይህ *መልካም ሥራ* ክርስቲያኖችንም፣ ክርስቲያን ያልሆኑትንም እንደሚያካትት ግልጽ አድርጎታል። "ስለዚህ ዕድሉ ካለን ለሰው ሁሉ፣ በተለይም ለእምነት ቤተ ሰቦች *መልካም* እናድርግ።" (ገላ. 6፥10)። "ማንም በከፉ ፈንታ ክፉ እንዳይመልስ ተጠንቀቁ፤ ነገር ግን እርስ በርሳችሁም ሆነ ለሌሎች ሰዎች ሁል ጊዜ *መልካም* የሆነ ውን ነገር ለማድረግ ተጣጣሩ።" (1ተሰ. 5፥15)።

ክርስቶስ አደጋ ሊኖረው በሚችል ቸርነት ከፍ ከፍ ይላል

እግዚአብሔር ለሕዝቡ ያለው የመጨረሻ *ዐላማ* የእርሱን ታላቅ ነት ማክበር እና የልጁን የኢየሱስ ክርስቶስን ዋጋ ከፍ ከፍ ማድረግ ነው። "እንግዲህ ስትበሉም ሆነ ስትጠጡ፣ ወይም ማንኛውንም ነገር ስታደርጉ፣ ሁሉንም ነገር ለእግዚአብሔር ክብር አድርጉት።" (1ቆሮ. 10፥31)። "ጽኑ ናፍቆቴና ተስፋዬ... በሕይወትም ሆነ በሞት ክርስቶስ በሥጋዬ እንዲከበር ነው።" (ፊል. 1፥20፣ የራሴ ትርጉም)። እግዚአብ ሔር በሁሉም ነገር ይከብራል፤ ክርስቶስ በሕይወትና በሞት ከፍ ከፍ

ይላል። ይህ ታላቁና ከእግዚአብሔር ለሰው ልጆች ሁሉ የተሰጠ የሕይወት ዐላማ ነው።

ስለዚህ በዚህ የኮሮናቫይረስ ወረርሽኝ ወቅት አንዱ የእግዚአብሔር ዐላማ የራሱ ሕዝብ ፍርሀትን እና ለራስ ያለ ሐዘኔታን ገድለው በአደጋ ፊትም ቢሆን ራሳቸውን ለመልካም ሥራ እንዲሰጡ ነው። ክርስቲያኖች፣ ከምቾት ይልቅ ወደ መሠረታዊ ፍላጎቶች፣ በግለኝነት ከአደጋ ነጻ ከመሆን ይልቅ ወደ ፍቅር ያዘነብላሉ። አዳኛችን ይህን ይመስላል ፤ የሞተውም ለዚህ ነው።

የመጀመሪያዋ ቤተ ክርስቲያን ምሳሌ

ሮድኒ ስታርክ *የክርስትና ድል (The Triumph of Christianity)* በሚለው መጽሐፉ በመጀመሪያው ክፍለ ዘመን በነበረችው ቤተ ክርስቲያን አስመልክቶ ሲጽፍ እንዲህ አለ፦ “የክርስትና ፍቅር እና ልግስና ከቤተሰብና ከእምነት ድንበሮች ውጪ ለሆኑ ለተቸገሩ ሁሉ መስፋፋት አለበት የሚለው እውነተኛ ሥር ነቀል መርሕ ነበራት።”[6]

በ165 እና 251 ዓ.ም. የሮማውያን ግዛቶች በሁለት ታላላቅ ወረርሽኞች ተመተው ነበር። በወቅቱ ከቤተ ክርስቲያን ውጪ ምንም ዐይነት የምሕረትና የመሥዋዕት ባህላዊም ሆነ ሃይማኖታዊ መሠረት አልነበረም። “አማልክት ለሰው ልጆች ጉዳይ ይጠነቀቃሉ የሚል እምነት አልነበረም።”[7] “ምሕረት እንደ ባሕርይ ጉድለት፣ ርኅራኄ እንደ ሥነ ልቦናዊ ችግር ይቁጠሩ ነበር፤ ምክንያቱም ምሕረት የማይገባንን ዕገዛን ወይም እፎይታን መስጠት ነውና፣ ይህም የፍትሕ ተቃራኒ ነው በማለት ያምናሉ።”[8]

ስለዚህ የግዛቱ ሚሶ ከበሽታው የተነሣ በመጥፋት ላይ እያለ የሕክምና ባለሙያዎች ወደ ሀገራቸው ሸሽተው ነበር። የበሽታውን ምልክት ያሳዩ ሰዎች ከየቤቱ ተባርረዋል፤ ካህናት ቤተ መቅደሶቻቸውን ትተዋል። ስታርክ ትዝብቱን ሲናገር ግን "ክርስቲያኖች መልስ እንዳላቸው ተናግረ ዋል፤ ደግሞ ተገቢውን ርምጃ ወስደዋል።"[9]

መልሶቹ በክርስቶስ በኩል የኃጢአት ስርየትን እና ከሞት በኋላ ያለውን የዘላለም ሕይወትን ያካትታሉ። ይህ በሕክምና ርዳታ በማይገኝ በትና ፍጹም ተስፋ በሚቈረጥበት ወቅት እጅግ ውድ መልእክት ነው።

ለርምጃዎቹ ደግሞ ብዙ ቀኖጥር ያላቸው ክርስቲያኖች ለታመሙት እና ለሚሞቱት እንክብካቤ ያደርጉ ነበር። በሁለተኛ ወረርሽኝ መገባደጃ አከባቢ የእስክንድርያው ቄስ ዲዮናስዮስ የቤተ ክርስቲያኑን አባላት እያሞገሰ ደብዳቤ ጽፎ ነበር፦

> "አብዛኛዎቹ ወንድሞቻችን ያልተገደበ ፍቅር እና ታማኝነት ያሳዩ ነበር፤ ራሳቸውን ሳይተዉ አንዱ ለሌላ ብቻ ያስብ ነበር። አደጋን ሳይፈሩ የታመሙትን እየተንከባከቡ ፍላጎቶቻቸውን ሁሉ እያ ሚሉ በክርስቶስ ያገለግሏቸው ነበር። ከእነርሱ ጋርም በተረጋጋ ደስታ ከዚህ ሕይወት ተለዩ።[10]

የነገሥታትን አላዋቂነት ጸጥ ማድረግ

ከጊዜ በኋላ ይህ ከባህል ጋር የተቃረነ እና በክርስቶስ የሆነ ሕሙማን እና ድኾችን መንከባከብ ብዙ በአከባቢው የነበሩ ሰዎችን ከአረማዊነት ሕይወት በማውጣት ታድጓል። ከሁለት ክፍለ ዘመን በኋላ የሮም ንጉሥ ዩሊያ (ጁሊያን) (332-363 ዓ.ም.) የጥንታዊውን የሮም

ሃይማኖት ወደ ሕይወት ለመመለስ ሲፈልግ፣ ክርስትናን እያደገ እንደ መጣ ሥጋት አይቶት ነበር። በዚህም ጭንቀት በገላትያ ለሚገኘው የሮማውያን ሊቀ ካህን ደብዳቤ ጽፎ ነበር፦

> ከሐዲነት [ማለትም የክርስትና እምነት] በተለየ ሁኔታ የተስፋፋው ለእንግዳ ሰዎች በሚሰጥ የፍቅር አገልግሎት እና ለሚሞቱ በሚደረግ እንክብካቤ ነው። አንድም አይሁዳዊ ለማኝ አለመኖሩ እና እነዚያ አምላክ የለሽ የገሊላ ሰዎች [ማለትም ክርስቲያኖች] ለራሳቸው ድኾች ብቻ ሳይሆን ለእኛም ድኾች እንክብካቤ ማድረጋቸው አሳፋሪ ነው። የእኛ የሆኑት ለእነርሱ ልንሰጥ የሚገባውን ርዳታ እንደ ከንቱ ነገር ያዩታል።[11]

ከእግዚአብሔር የተላከ መከራን ማስታገሥ

ኮሮናቫይረስን እንደ እግዚአብሔር ሥራ በማየትና የሚያመጣውን ሥቃይ ለመቀነስ ክርስቲያኖች ኀላፊነትን እንዲወስዱ ጥሪ በማድረግ መካከል ምንም የሚጋጭ ነገር የለም። እግዚአብሔር በውድቀት ዓለምን ለሥቃይና ኃጢአት ከዳረገ ጀምሮ፣ ምንም እንኳ የጥፋትን ፍርድ የወሰነው እርሱ ቢሆንም፣ የእርሱ ሕዝቦች ከጥፋት ለመዳን እንዲሹ አዝዟል። እግዚአብሔር ራሱ ከራሱ የፍትሕ ፍርድ ሰዎችን ያድን ዘንድ በክርስቶስ ኢየሱስ ወደ ዓለም መጣ (ሮሜ 5፥9)። የክርስቶስ መስቀል ማለት ይህ ነው።

ስለዚህ የእግዚአብሔር ሰዎች መልካም ሥራዎች የታመሙት እንዲፈወሱ፣ እግዚአብሔር እጁን እንዲዘረጋና ወረርሽኙን እንዲያቆመውና መድኀኒትን እንዲሰጠን መጸለይን ያካትታል። ስለ ኮሮናቫይረስ

እንጸልያለን ደግሞም የመከራውን ሥቃይ ለመቀነስ እንሠራለን። ልክ አብርሃም ሊንከን እንደ እግዚአብሔር ፍርድ የተመለከተውን የርስ በርስ ጦርነት ለማቆም እንደ ጸለየውና ለማቆም እንደ ሠራው፡-

> “ይህ ታላቅ የጦርነት መቅሠፍት በፍጥነት እንዲያልፍ ተስፋ እና ደርጋለን…አጥብቀንም እንጸልያለን። ሆኖም ግን እግዚአብሔር እንዲቀጥል ከፈቀደ፣ ለሁለት መቶ ኀምሳ ዓመታት በባርነት ትጋት በጠንካራ መሠረት ላይ የተተከለው ከባድ የሀብት ምሰሶ እስኪሰምጥ ድረስ፣ ባረፈባቸው ጅራፍ የፈሰሰው እያንዳንዱ የደም ጠብታ ዋጋውን በተመዘዘ ሌላ ሰይፍ እስኪቀ በል ድረስ፣ ከሦስት ሺሕ ዓመት በፊት የተነገረው ዛሬም ሊነገር ይገባል፡- “የእግዚአብሔር ፍርድ የታመነ፣ ሁለንተናውም ጻድቅ ነው፤”

እግዚአብሔር የሚሠራው ሥራ አለው—አብዛኛው ግን ምስጢራዊ ነው። እኛም የራሳችን ሥራ አለን። በእርሱ የምንታመንና ቃሉን የምንታዘዝ ከሆነ ሉዓላዊነቱ እና አገልግሎታችን የእርሱን ጥበብና መልካም ዐላማዎች እንዲፈጽሙ ያደርጋል።

ምዕራፍ 11

ሕዝብን ለመድረስ ሥርን ማላላት

መልስ 6

እግዚአብሔር በኮሮናቫይረስ ውስጥ በመላው ዓለም በአንድ ቦታ ተመቻችተው የተቀመጡ ክርስቲያኖችን ለዐዲስና ሥር ነቀል ለሆነ ነገር ነጻ ለማድረግ እና ወዳልተደረሱ የዓለም ህዝቦች ከክርስቶስ ወንጌል ጋር ለመላክ በአንድ ሰፍራ የተንሰራፋውን ሥራቸውን እያላላ ነው።

ኮሮናቫይረስን ከወንጌል ተልእኮ ጋር ማገናኘት እንግዳ ሐሳብ ሊመስል ይችላል፤ ምክንያቱም ኮሮናቫይረስ በዐጭር ጊዜ ውስጥ ጉዞዎችን፣ ፍልሰቶችንና የሚስዮንን እድገት አስተጓጉሏል። ነገር ግን እኔ እያሰብሁ ያለሁት ስለ ዐጭር ጊዜ አይደለም። እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያንን መሄድ ወዳለባት ስፍራ ለማንቀሳቀስ በታሪክ ውስጥ

መከራን እና ሁከትን ተጠቅሟል። እኔ እየጠቁምሁኝ ያለሁት፣ በኮሮና ቫይረስ የረጅም ጊዜ ተጽዕኖ፣ ቤተ ክርስቲያንን በድጋሚ ማንቀሳቀሻ ያደርግ ይሆናል ብዬ ነው።

ስደት እንደ ሚስዮናዊ ስልት

ለምሳሌ እግዚአብሔር ሕዝቡን በተልእኮ እንዴት ከኢየሩሳሌም ወደ ይሁዳና ሰማርያ እንዳንቀሳቀሰ ዐስቡ። ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን ወንጌልን ወደ ዓለም ሁሉ እንዲያደርሱ አዘዛቸው "በኢየሩሳሌም፣ በይሁዳና በሰማርያ ሁሉ፣ እስከ ምድር ዳርቻ ድረስ"። ነገር ግን በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 8 ጊዜ በኢየሩሳሌም ተገድቦ የነበረ ይመስላል።

ቤተ ክርስቲያንን ወደ ተልእኮዋ ለመመለስ ምን ያስፈልጋል? የእስጢፋኖስን ሞትና መሞቱን ተከትሎ የመጣ ስደት አስፈልጓት ነበር። እስጢፋኖስ ሰማዕት እንደ ሆነ (ሐ.ሥ. 7፥60) ስደት ተቀሰቀሰ፡-

> "በዚያ ቀን በኢየሩሳሌም በነበረችው ቤተ ክርስቲያን ላይ ታላቅ ስደት ተነሣ፤ ከሐዋርያትም በስተቀር አማኞች በሙሉ በይሁዳና በሰማርያ አውራጃዎች ሁሉ ተበተኑ፤ ...የተበተኑትም በሄዱበት ሁሉ ቃሉን ሰበኩ፤" (ሐ.ሥ. 8፥1-4)

እግዚአብሔር ህዝቡን ማንቀሳቀስ የቻለው በሰማዕትነት እና በስደት ነበር። በመጨረሻ "ይሁዳና ሰማርያ" ወንጌል ሰሙ። የእግዚአብሔር መንገድ የእኛ መንገድ አይደለም። ተልእኮው ግን እርግጥ ነው። ኢየሱስም እንደዚያ ብሏልና ቃሉ ደግሞ ሊወድቅ አይችልም። "በዚህ ዐለት ላይ ቤተ ክርስቲያኔን እሠራለሁ፤ የገሃነም ደጆችም አያሸንፏትም"

(ማቴ. 16፥18)። “ለሕዝብ ሁሉ ምስክር እንዲሆን፣ ይህ የመንግሥት ወንጌል በዓለም ሁሉ ይሰበካል” (ማቴ. 24፥14)። “ይሰበክ ይሆናል” ሳይሆን “ይሰበካል”።

ማነቆን እንደ ስልታዊ እድገት

የኮሮናቫይረስ ወረርሽኝ ለዓለም ዐቀፉ የወንጌል ተልእኮ ማነቆ፣ እንቅፋት እንደሆነ እናስብ ይሆናል። እኔ ግን እጠራጠራለሁ። ብዙ ጊዜ የእግዚአብሔር አሠራሮች በግልጽ የሚታዩ መሰናክሎችን ያካትታሉ፣ ይሁንና በአብዛኛው ትልልቅ እድገቶችና ውጤታማ ሥራዎች ከመሰና ክሎቹ በኋላ ይፈጸማሉ።

በጥር 9 ቀን 1985 ቡልጋሪያ ውስጥ መጋቢ ሄሪስቶ ኩልቼቭ የተባለ የአንዲት አጥቢያ መጋቢ ታስሮ ነበር። የፈጸመው ወንጀል ደግሞ በአጥቢያዋ ሳይሆን በመንግስት የተሾመ መጋቢ እያለ እርሱ መስበኩ ነበር። የርሱ የፍትሕ ሂደት ፍትህን አሰዳቢ ነበር። ስምንት ወር እስራት ተፈረደበት። በእስር ቤት በነበረበት ወቅት ክርስቶስን ማሳወቅ በሚች ልበት መንገድ ሁሉ አሳውቋል።

ከእስር ሲፈታ አንዲህ ጻፈ፦ “እስረኞቹም ሆኑ የእስር ቤቱ ጠባቂ ዎች ብዙ ጥያቄ ይጠይቁ የነበረ ሲሆን፣ በቤተ ክርስቲያን ይሆናል ብለን ከምንጠብቀው የበለጠ ፍሬያማ አገልግሎት እንዳገኘን ተገለጠ። እግዚ አብሔርን ከእስር ነጻ ሆነን ከምናገለግለው በተሻለ በእስር ቤት በመገኘታችን አገለገልነው።”[12] ይህ ብዙውን ጊዜ የእግዚአብሔር መንገድ ነው። የኮሮናቫይረስ ዓለም ዐቀፍ ስፋትና አሳሳቢነት ለእግዚአብሔር

የማያባክነው ትልቅ ነገር ነው። የማይበገረውን ዓለም ዐቀፋዊ ወንጌል የማዳረስን ዐላማ ያሳካበታል። ክርስቶስ ደሙን በከንቱ አላፈሰሰም። ራእ. 5፥9 በደሙ “ከነገድ ሁሉ፣ ከቋንቋ ሁሉ፣ ከወገን ሁሉ፣ ከሕዝብ ሁሉ ሰዎችን ለእግዚአብሔር” ዋጀ ይላል። የመከራውን ሽልማት እርሱ ያገኛል። ዓለም ዐቀፍ ወረርሽኞችም ሳይቀሩ ታላቁ ተልእኮን ለመፈጸም ያገለግላሉ።

የማጠቃለያ ጸሎት

አባት ሆይ፣

በጣም ጥሩ በሆነው ጊዜያችን፣ በአንተ ጸጋ በጌቴሴማኒ አልተኛ ንም። ነቅተን የልጅህን ጸሎት እየሰማን ነው። መሠቃየቱ ግድ እንደ ሆነ በርግጥ ያውቃል፤ ነገር ግን ፍጹም በሆነው ሰብኣዊነቱ፣ “ቢቻል ይህ ጽዋ ከእኔ ይለፍ” በማለት ጮኸ።

በተመሳሳይ መንገድ ይህ ወረርሽኝ በጥበብህ ለበጎና፣ አስፈላጊ ለሆኑ ዐላማዎች እንደተላከ በርግጥ እንረዳለን። እኛ መከራ ልንቀበል ይገባናል። ልጅህ ንጹሕ ነበር፤ እኛ ግን አይደለንም።

ሆኖም ግን ፍጹም ባልሆነው ሰብኣዊነታችን ከእርሱ ጋር “ቢቻል ይህ ጽዋ ይለፍ” ብለን እንጮኻለን። ጌታ ሆይ ለመሥራት የወሰንከውን የሚያሳምም፣ ፍትሓዊ እና የምሕረት ሥራ ፈጥነህ አከናውን። በፍርድህ አትዘግይ። ርኅራኄህን አታዘግየው። ጌታ ሆይ እንደ ምሕረትህ ድኾችን ዐስብ። የተጐሳቈሉ ሰዎችን ጩኸት አንዘንጋ። ከሕመም ማገገምን ስጠን። መድኀኒትን ስጠን። ድኻና ምስኪን የሆንን የአንተ ፍጥረቶች ከዚህ ሐዘናችን ትታደገን ዘንድ እንጸልያለን።

ነገር ግን ጌታ ሆይ መከራችንና ሐዘናችን አይባክን። ሕዝብህን ባዶ ከሆነ ቍሳዊነትና ክርስቶስ አልባ ከሆነ ኀይል የለሽ የተዝናኖት ሐሳብ አጽዳ። የሰይጣንን የማታለያ ምግብ አፋችን እንዳያጣጥም አድርገው።

የትዕቢት፣ የጥላቻንና የኢፍትሓዊነት ሥርን እና ርዝራዥን ከኛ ቍረጥ። ክብርህን ዝቅ በምናደርግ በራሳችን ላይ የመቄጣት ዐቅምን ስጠን። የክርስቶስን ውበት እንድናይና እንድናጣጥም የልቡናችንን ዐይኖች ክፈት። ልባችንን ወደ ቃልህ፣ ወደ ልጅህና ወደ መንገድህ አዘንብለው። በርኅራኄ ብርታት ሙላን። ሕዝብህ በሚያገለግልህ መንገድ ስምህን አድምቀው። ለሚጠፋው ለዚህ ዓለም ስትል እጅህን ለታላቅ ማንቂያ ዘርጋ። "አሁንም ከእጃቸው ሥራ ንስሓ አልገቡም" የሚለው አስጨና ቂው የራእይ መጽሐፍ ቃላት በዚህ ትውልድ ላይ አይነገር። አካልን እንደ ጐሰምኸው አሁን ደግሞ የተኙትን ነፍሳት ጐስመኽ አንቃ። በትዕ ቢትና እምነት በማጣት ጨለማ ውስጥ ከመተኛት ይከልከሉ። በታላቅ ምሕረትህ "በሕይወት ኑሩ" በልና በሚሊዮን የሚቈጠሩ ልቦችና ሕይ ወቶች ወደር በማይገኝለት በኢየሱስ ዋጋ ወደ መስተካከል ይምጡ።

በኢየሱስ ስም! አሜን።

ማስታወሻ

1 “1918 Pandemic (H1N1 Virus),” updated March 20, 2019, Centers for Disease Control and Prevention, https://www.cdc.gov/flu/pandemic-resources/1918-pandemic-h1n1.html

2 Henry Martyn, Journals and Letters of Henry Martyn (New York: Protestant Episcopal Society, 1861), 460.

3 Martyn, Journals and Letters, 210.

4 John Lennon, “Imagine,” produced by John Lennon, Yoko Ono, and Phil Spector, Abbey Road, London, 1971.

5 C. S. Lewis, “The Weight of Glory,” in The Weight of Glory and Other Addresses (1949; repr., New York: Harper, 2009), 26.

6 Rodney Stark, The Triumph of Christianity: How the Jesus Movement Became the World’s Largest Religion (New York: Harper, 2011), 113

7 Stark, Triumph of Christianity, 115.

8 Stark, Triumph of Christianity, 112.

9 Stark, Triumph of Christianity, 116.

10 Stark, Triumph of Christianity, 117.

11 Stephen Neill, A History of Christian Missions, 2nd ed. (New York: Penguin, 1986), 37–38.

12 Herbert Schlossberg, Called to Suffer, Called to Triumph (Portland, OR: Multnomah, 1990), 230.

desiringGod

እግዚአብሔርን መፈለግ

ሁሉም ሰው ደስተኛ መሆን ይፈልጋል። ድረ ገጻችን የተወለደውና የተገነባው ለደስታ ነው። በእግዚአብሔር እጅግ ስንረካ እርሱ ደግሞ በእኛ እጅግ ይከብራል። ይህን እውነት በየትም ያሉ ሰዎች ሁሉ እንዲረዱትና አጥብቀው እንዲይዙት እንፈልጋለን። ከአርባ ቋንቋዎች በላይ የተተረጐሙትንም ጨምሮ፣ የጆን ፓይፐርን ከሠላሳ ዓመት በላይ በንግ ግርና በጽሑፍ የተዘጋጁ ትምህርቶችን አሰባስበናል። እንዲሁም የማያ ልቀውን እውነት፣ ዐላማና ርካታ እንዲያገኙ የሚረዱ ዐዳዲስ የጽሑፍ፣ የድምፅ እና የምስል ግብአቶችን እናቀርባለን። እነዚህ ሁሉ ትምሕርቶች በነጻ በድረ ገጻችን ላይ መቅረብ የቻሉት፣ በአገልግሎቱ የተባረኩ ሰዎች ለአገልግሎቱ ሥራ በልግስና ስለሚሰጡ ነው።

ለእውነተኛ ደስታ የሚሆኑ ተጨማሪ መረጃዎችን ከፈለጉ ወይም በ “ዲዛየሪንግ ጋድ” (እግዚአብሔርን መፈለግ አገልግሎት) ስለምናከና ውናቸው ሥራዎች ተጨማሪ ማወቅ ከፈለጉ፣ ድረ ገጻችንን እንዲጐበኙ እንጋብዛለን።

---

desiringGod.org

“ይህ ጊዜ የዚህ ዓለም ተሰባሪነትና ተንኮታኳችነት ውስጣችን ገብቶ የተሰማበት ጊዜ ነው። ጽኑ የሚመስሉ መሠረቶች እየተናወጡ ነው። ልንጠይቀው የሚገባ ጥያቄ፣ በአግሮቻችን የቆምንበት ዐለት አለን ወይ? ለመቼውም የማይናወጥ ዐለት? የሚለው ነው።”

ጆን ፓይፐር

እ.አ.አ. ጃንዋሪ 11, 2020 (ጥር 2 ቀን 2012 ዓ.ም) ከዚህ ቀደም ማንም የማያውቀው ዐዲሱ ኮሮናቫይረስ (ኮቪድ-19) የመጀመሪያው ሰለባ ዉሃን በተባሉች የቻይና ክፍለ ሀገር መሆኑ ሪፖርት ተደረገ። ማርች 11, 2020 (መጋቢት 2 ቀን 2012 ዓ.ም.) ደግሞ በዓለም ጤና ድርጅት ዓለም አቀፍ ወረርሽኝ ተብሎ ታወጀ። በዚህ ፍርሀትና ‘ከዚህስ በኋላ ምን ይመጣ ይሆን?’ በሚል ስጋት ውስጥ ‘እግዚአብሔር ምን እያደረገ ነው?’ ብሎ መጠየቁ ተፈጥሮአዊ ነው።

ኮሮናቫይረስ እና ክርስቶስ በተሰኘው መጽሐፋቸው፣ ጆን ፓይፐር፣ በዓለም ዙሪያ ያሉትን አንባቢዎቻቸውን በሁሉም ነገር ላይ አስቀድሞ ወሳኝ፣ ግዙ እና ንጉሥ በሆነው፣ ጠቢብ እና መልካም የሆነውን ዓላማውንም በእርሱ ለሚያምኑት ሁሉ በሚፈ ጽመው፣ ጽኑ ዐለት በሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ እንዲቆሙ ይጋብዛሉ። “እግዚአ ብሔር በኮሮናቫይረስ ምን እየሠራ ነው?” ለሚለው ጥያቄ ጆን ፓይፐር ስድስት መጽሐፍ ቅዱሳዊ መልሶችን በመስጠት፣ በዚህ ባለንበት ታሪካዊ ጊዜ እግዚአብሔር በመካከላችን ማከናወን የሚፈልገውን እየሠራ እንደሆነ ያስታውሱናል።

ጆን ፓይፐር ዲዚየሪንግ ጋድ (desiringGod.org) በመባል የሚታወቀው አገልግ ሎት መሥራችና መሪ አስተማሪ እንዲሁም የቤተልሔም ኮሌጅና ስነ-መለኮት ትምህርት ቤት (ሴሚናሪ) ጎላፊ ናቸው። ለሠላሳ ሦስት ዓመታት በሚኒያፖሊስ፣ ሚነሶታ የምትገ ኘውን የቤተልሔም ባፕቲስት ቤተ ክርስቲያንን በመጋቢነት አገልግለዋል። Desiring God (እግዚአብሔርን መፈለግ)፣ Don’t Waste Your Life (ሕይወትህን አታባክን) እና Reading the Bible Supernaturally (መጽሐፍ ቅዱስን ልዕለ ተፈጥሮአዊ በሆነ መንገድ ማንበብ) በመባል የሚታወቁትን ጨምሮ፣ ከጎምሳ በላይ መጻሕፍት የጻፉ ናቸው።

CROSSWAY
crossway.org